https://chilot.me

የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግስት

ደቡብ ነጋሪት ጋዜጣ

DEBUB NEGARIT GAZETA

OF THE SOUTHERN NATIONS, NATIONALITIES AND PEOPLE'S REGIONAL STATE

15ኛ ዓመት ቁጥር 1

ሀዋሳ ጥቅምት 20 ቀን 2001ዓም

በደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል

መንግሥት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፫፫/፳፻፩ ዓ/ም

የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግስት የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያና የግብርና ሥራ ገቢ ግብር ደንብ ቁጥር ፻፷/፪፷፻ ..... ገፅ ፩

መ ግ ቢ ያ

የክልሉ መንግስት የአርሶአደሩና የአርብቶአደሩ የግብር አከፋፈል ሥርዓት ይበልጥ ፍትሃዊ ለማድረግ እንዲቻል የግብር አጣጣል ይዘቱን በማሻሻል አዲስ የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያና የግብርና ስራ ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር ፻፷/፪፷፻ ያወጣ በመሆኑ፣

ይህንን የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያና የግብርና ስራ ገቢ ግብር አዋጅ ተግባራዊ ለማድረግና ለህብረተሰቡ የግብር ግዴታውን በተሟላ ሁኔታ ለማሳወቅ የሚያስችል ዝርዝር ጉዳዮችን የያዘ ማስፈፀሚያ ደንብ ማውጣት በማስፈለጉ፣

አርሶ አደሩም ሆነ አርብቶ አደሩ መብቱንና ግዴታውን አውቆ በያዘው የመሬት ይዞታ ስፋትና በሚረባው የእንስሳት ብዛት መጠን ትክክለኛና ፍትሃዊ ግብር በወቅቱ መክፈል እንዲችል ለማድረግ፣

አዋጁን ለማስፈፀም ግልጽ መሆን የሚገባቸውን ልዩ ልዩ ድንጋጌዎችን ለይቶ በማመልከት በአፈፃፀም ሂደት ሊከሰቱ የሚችሉ የተሳሳቱ ግንዛቤዎችንና አሠራሮችን ለመቅረፍ የሚያስችል በመሆኑ፣

የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግስት መስተዳድር ም/ቤት በክልሉ ሕገ-መንግስት አንቀፅ ፶፮ ንዑስ አንቀፅ ፮ እና የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያና የግብርና ሥራ ገቢ ግብር እንደገና ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፱፸፪/፸፱ አንቀፅ ፸፪ መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌዎች

፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያና የግብርና ሥራ ገቢ ግብር ደንብ ቁጥር ፫፲/፸፱፩ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪.ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ሆኖ ካልተገኘ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩ ‹‹**አዋጅ**›› ማለት የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያና የግበርና ሥራ ገቢ ግብር እንደገና ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር ፱፸፪/፸፱ ነው፡፡

፪ ‹‹**የይዞታ ባለቤትነት መብት**›› ማለት ማንኛውም አርሶ አደር ወይም ከፊል አርብቶ አደር የገጠርን መሬት ለግብርና ልማት ተግባር ለማዋል፣ ለማከራየት፣ በህግ መብት ለተሰጣቸው ወራሾች ለማውረስ የሚኖረው መብት ሲሆን፣ በመሬቱ ላይ በጉልበቱ ወይም በገንዘቡ ንብረት የማፍራትና ይህንንም ንብረት የመሸጥ፣ የመለወጥና የማውረስ መብት ይጨምራል፡፡

፫ ‹‹**የቤተሰብ አባል**›› ማለት የይዞታ ባለመብቱን መተዳደሪያ ገቢ በመጋራት በቋሚነት አብሮ የሚኖር ማንኛውም ሰው ነው፡፡

፬ ‹‹**ሞግዚት**›› ማለት ለአካለ መጠን ያልደረሱና ወላጆቻቸውን በሞት ወይም በሌላ ምክንያት ያጡ ልጆችን የሚያሳድግ ሕጋዊ ሰው ነው፡፡

፭ ‹‹**የቀንድ ከብቶች**›› ማለት ጊደር፣ ወይፈን፣ ላም፣ በሬ፣ በግና ፍየል ነው፡፡

፮ ‹‹**የግል የመሬት ይዞታ**›› ማለት በአርሶ አደር፣ በከፊል አርብቶ አደር ወይም በሌላ በሕግ መብት በተሰጠው አካል በግል ይዞታነት ተመዝግቦ የሚገኝ የገጠር መሬት ነው፡፡

፯ ‹‹**የወል መሬት**›› ማለት ከግል ይዞታነት ውጪ የሚገኝና የአካባቢ ነዋሪዎች በጋራ ይዞታነት የሚጠቀሙበት የገጠር መሬት ሆኖ በተለይም ለግጦሽ፣ ለደን ልማት፣ ለማዕድን ማምረት፣ ለጎዳና እና ለተለያዩ ማህበራዊ አገልግሎቶች እየዋለ የሚገኝ የገጠር መሬት ነው፡፡

፰ ‹‹**በመንግስት ይዞታ ስር የሚገኝ መሬት**›› ማለት የውል መሬትን ጨምሮ ማንኛውም በግል ይዞታነት ያልተመዘገበና በማንኛውም አካል የገቢ ግብር እና የመጠቀሚያ ክፍያ ወይም የመሬት ኪራይ ያልተከፈለበት የገጠር መሬት ነው፡፡

፱ ‹‹**ለመስኖ ልማትና የኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸው ሰብሎች ለማምረት የዋለ መሬት**›› ማለት በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፭፪ ላይ የተመለከቱት ሰብሎችን በጣምራ ወይም በተናጠል ለማልማት የዋለ በግል ይዞታነት የተመዘገበ የገጠር መሬት ነው፡፡

፲ ‹‹**ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸው ሰብሎች**›› ማለት በአዋጅ ፪ ከንዑስ አንቀፅ ፲፫-፲፮ ከተጠቀሱት ሰብሎች በተጨማሪ የተለያዩ ቅመማ ቅመሞችን ለምሳሌ ዝንጅብል፣ ኮረሪማ፣ እርድ ነጭና ጥቁር አዝሙድ፣ ሻይቅጠል፣ ሄል፣ቀረፋ እና ቁርንፉድ ሰብሎችን ያካተተ ነው፡፡

፲፩.‹‹**ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸው አምራች**›› ማለት በአዋጁ በአንቀፅ ፪ ከንዑስ አንቀፅ ፲፫-፲፮ ከተጠቀሱት ሁኔታ በተጨማሪ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፲ ላይ የተመለከቱት ሰብሎችን በአንድ ስምንተኛ (1/8) ሄክታር ወይም ከዚህ በላይ ስፋት ባለው ይዞታው ወይም በተከራየው የገጠር መሬት ላይ የሚያመርት እንዲሁም በአንድ አራተኛ (1/4) ሄክታር የመሬት ስፋት ላይ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸው ሰብሎችን በጣምራ (በማፈራረቅ ወይም በማዳበል) በመዝራት ወይም በመትከል ምርቶቹን ወይም ችግኞቹን እያመረተ ለገበያ በማቅረብ የሚጠቀም አርሶአደር ነው፡፡

፲፪. ‹‹**ለመደበኛ እርሻ ሥራዎች የዋለ የገጠር መሬት ይዞታ**›› ማለት በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ ፲፩ ከተጠቀሰው ሁኔታ ውጭ ሌሎች ወቅታዊና ዓመታዊ ሰብሎች ለማምረት፣

ሌሎች ቋሚ ሰብሎች ለማልማት፣ ለሳርና ለግል ግጦሽ ጠቀሜታ የዋለ፣ በሰው ሠራሽ ወይም በተፈጥሮ ደን የተሸፈነ በቁጥቋጦና በሸለቆ የተሸፈነ፣ ድንጋያማና ቦረቦር የሆነ የገጠር መሬት ነው፡፡

፲፫. ‹‹**የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ደብተር**›› ማለት በገጠር መሬት የመጠቀምን መብት ለማረጋገጥ አግባብ ባለው የክልሉ መንግስት አካል የሚሰጥ የገጠር መሬት የይዞታ ባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ ነው፡፡

፲፬. ‹‹**የመሬት ምዝገባ**›› ማለት በገጠር መሬት የመጠቀምና የባለይዞታነት መብት ያለቸው አካላት ለይቶ ለመመዝገብና ዕውቅና ለመስጠት የሚያስችል መረጃ የማሰባሰብና የማጠናቀር ሂደት ነው፡፡

፲፭. ‹‹**መሠረተ ግምት**›› ማለት በአንድ ቀበሌ፣ በአንድ ወረዳ በአንድ ዞን ወይም በአጠቃላይ በክልሉ ከሚገኙ ግብር ከፋይ የገጠር መሬት የይዞታ ባለቤት ከሆኑ አርሶአደሮች እና የእንስሳት እርባታ ባለቤት ከሆኑ አርብቶአደሮች በአንድ የበጀት ዓመት የሚሰበሰብ የገቢ ግብር እና የመጠቀሚያ ክፍያ ጠቅላላ ድምር ነው፡፡

፲፮. ‹‹**የግመታ አስተባባሪ ኮሚቴ እና የገማች ኮሚቴ**›› ማለት በገጠር ቀበሌ የመሬት ይዞታቸውን ወይም የእንስሳት እርባታቸውን (ለአርብቶአደር አካባቢዎች ብቻ) በወቅቱ ሳያስታውቁ የቀሩ ወይም አሳንሰው ያስታወቁ ነዋሪዎች የይዞታቸውን መጠን ወይም የእንስሳት እርባታቸውን ብዛት ገምቶ የሚያቀርብ እንደቅደምተከተሉ በቀበሌ ደረጃ እና በልማታዊ ቡድን ደረጃ የሚገኘው የአመራር አካል ነው፡፡

፲፯. በዚህ ደንብ በወንድ ፆታ የተገለፁት ለሴት ፆታም ያገለግላል፡፡

፲፰. በዚህ ደንብ ውስጥ የተለየ ትርጉም ያልተሰጣቸው ሌሎች ቃላቶችና ሐረጎች በአዋጁ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡

፫. <u>የደንቡ የተፈፃሚነት ወሰን፡-</u>

፩ ይህ ደንብ በደ/ብ/ብ/ሕዝቦች ክልል መንግስት ውስጥ በሚገኝ የገጠር መሬት የግብርና ልማት ሥራ በተሠማሩ አርሶ አደሮችና ከፊል አርብቶአደሮች፣ በእንስሳት እርባታ ሥራ በተሠማሩ አርብቶአደሮች እና በማናቸውም የግብርናም ሆነ

የኢንዱስትሪ ልማት ሥራ በተሠማሩ የመንግስት ወይም የግል ኢንቨስትመንቶች ላይ ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

፪ በአዋጁ አንቀፅ ፪ ንዑስ አንቀፅ ፩ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በክልሉ መንግስት የከተማነት ደረጃ በተሰጣቸው ከተሞች ዙሪያ የሚገኙና በከፊል ወይም በሙሉ በከተማው ስር በታቀፉ የገጠር ቀበሌዎች ውስጥ ነዋሪ የሆኑ የመሬት ባለይዞታዎችም ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

ክፍል ሁለት

የግብር ከፋዮች ምዝገባና የክፍያ መሠረታቸው ስለሚታወቅበት ሁኔታ

፬ **የግብር ከፋይ አርሶአደሮችና አርብቶ አደሮች የምዝገባ ሁኔታ እና የክፍያ መሠረታቸውን የሚያስታውቁበት አሠራር፣**

፩ በክልሉ በገጠር ቀበሌ በስሙ የተመዘገበ የመሬት ይዞታ ያለው ማንኛውም አርሶአደርና ከፊል አርብቶአደር ወይም የእንስሳት እርባታ ባለቤት የሆነ ማንኛውም አርብቶአደር በሚኖርበት ቀበሌ አስተዳደር ጽ/ቤት ቀርቦ በባለቤትነት የያዘውን የገጠር መሬት ይዞታ ስፋት ወይም የእንስሳት እርባታ ብዛት በአዋጁ በተደነገገው የጊዜ ገደብ ውስጥ በትክክል በማስታወቅ በግብር ከፋይነት የመመዝገብ ግዴታ አለበት፣

፪ የቀበሌው አስተዳደር በቀበሌው የመሬት ባለይዞታ ወይም የእንስሳት እርባታ ባለቤት የሆነ ማንኛውም ሰው በአዋጁ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ወስጥ በቀበሌው አስተዳደር ጽ/ቤት ቀርቦ መሬት ይዞታው ስፋት ወይም የእንስሳት እርባታው ብዛት በማስታወቅ በግብር ከፋይነት የመመዝገብ ግዴታ ያለበት መሆኑን ሕዝብ በሚበዛባቸው ቦታዎች በመቀስቀስ ግንዛቤ የማስጨበጥ ኃላፊነት አለበት፡፡

፫ የቀበሌው አስተዳደር በቀበሌው በስማቸው የተመዘገበ የመሬት ይዞታ ያላቸው አርሶአደሮችና ከፊል አርብቶአደሮች ወይም የእንስሳት እርባታ ባለቤት የሆኑ አርብቶ አደሮች ስም ዝርዝር በየመንደራቸው ለይቶ በቀበሌው የግብር ከፋዮች መዝገብ ላይ በቅድሚያ በማስፈር የክፍያ መሠረታቸውን ያስታወቁትን በየእለቱ

ተከታትሎ በማወራረስ የቀበሌው የመሬት ባለይዞታዎች ወይም የእስሳት እርባታ ባለቤቶች በሙሉ በአዋጅ የተጣለባቸው የክፍያ መሠረታቸውን በጊዜ ገደብና በትክክል የማስታወቅ ግዴታቸውን በአግባቡ እየተወጡ መሆኑን የመከታተልና የማረጋገጥ ኃፊነት አለበት፡፡

፬ በቀበሌው የመሬት ይዞታ ባለቤት የሆነ ማንኛውም ሰው ለቀበሌው የሚያስታውቀው የይዞታው መጠን ለመሬት ይዞታው ባለቤትነት ማረጋገጫ በተሰጠው ደብተር ላይ በተመለከተው መጠንና የሚሰጠው ጠቀሜታ በዝርዝር በመግለፅ ይሆናል፡፡

፭ በያዘው የይዞታ ማረጋገጫ ደብተሩ ላይ የተመለከተው የመሬት ስፋት በዝቷል ወይም አንሷል ተሻሽሎ ይመዝገብልኝ የሚል ጥያቄ የሚያቀርብ ባለይዞታ ቢኖር ይህንኑ ጥያቄው ደብተሩን ለሰጠው አካል አቅርቦና ተቀባይነት አግኝቶ የይዞታው ስፋት ተስተካክሎ ደብተሩ እስከሚለወጥ ድረስ በደብተሩ በተመለከተው የይዞታ ስፋት መጠን ተመዝግቦ የሚፈለግበትን የገቢ ግብር እና የመጠቀሚያ ክፍያ የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

፮ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ያልተሰጣቸው ባለይዞታዎች በቀበሌው በስማቸው የተመዘገበ የመሬት ይዞታ ስፋት መጠን በራሳቸው ግንዛቤ አስካሁን በሚያውቁት መሠረት በአካባቢው የመሬት መለኪያ አንባር ወይም በሄክታር ያላቸውን ጠቀሜታ በዝርዝር በመግለፅ የክፍያው መሠረት በወቅቱ ማስታወቅ ግዴታ አለባቸው፡፡

፯ አንድ አርሶአደር በሚኖርበት ቀበሌ ውስጥ በተለያዩ መንደሮች የሚገኙ የመሬት ይዞታዎች ያሉት እንደሆነ የይዞታዎቹ ስፋት፣ የሚገኙበት መንደር እና ያላቸው ጠቀሜታ በዝርዝር በመግለፅ በአንድ አጠቃሎ በቀበሌው አስተዳደር ጽ/ቤት ቀርቦ የማስታወቅ ግዴታ አለበት፣

፰ አንድ አርሶአደር በወረዳው በነዋሪነት ከሚታወቅበት ቀበሌ ውጪ ተጨማሪ የመሬት ይዞታዎች በአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ በወረዳው ቀበሌዎች ያሉት እንደሆነ እርሶአደሩ የመሬት ይዞታዎቹ በሚገኙበት በየቀበሌው አስተዳር ጽ/ቤት ተገኝቶ የይዞታው ስፋትና ያለው ጠቀሜታ በዝርዝር በመግለፅ በተናጠል የማስታወቅ ግዴታ አለበት፡፡

፱) አርሶአደሩ ከሚኖርበት ወረዳ ውጭ ተጨማሪ የመሬት ይዞታዎች ያሉት እንደሆነ ይዞታዎቹ በሚገኙበት ወረዳ በተናጠል የሚመዘገብ በመሆኑ አርሶአደሩ በየደረጃው ይዞታው በሚገኝበት ቀበሌ አስተዳደር ተገኝቶ የይዞታውን መጠንና የአጠቃቀሙን ሁኔታ በዝርዝር ገልፆ በተናጠል በማስታወቅ በግብር ከፋይነት የመመዝገብ ግዴታ አለበት፣

፲) በተናጠል በስማቸው የተመዘገበ የመሬት ይዞታ ወይም የእንስሳት እርባታ ያላቸው ባለትዳሮች የክፍያ መሠረታቸው በቀበሌው አስተዳደር ጽ/ቤት ተገኝተው በተናጠል በማስታወቅ የሚፈለግባቸውን የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያና የግብርና ሥራ ገቢ ግብር በተናጠል የመክፈል ግዴታ አለባቸው።

፲፩. እያንዳንዱ አርሶ አደር በቀበሌው በተለያዩ መንደሮች የሚገኙና በአንድ ቤተሰብ ስም የሚታወቁት የመሬት ይዞታዎች መጠንና የሚገኙበት አካባቢ በመጥቀስ የሚያስታውቀው በራሱ ግንዛቤ አስካሁን በሚያውቀው መሠረት በአካባቢው የመሬት መለኪያ ወይም በሄክታር ሆኖ ከመሬት ይዞታው ውስጥ ለመስኖ ልማት እና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸው ሰብሎች ለማምረት የዋለ የመሬት ስፋት እና ለመደበኛ እርሻ ሥራዎች የዋለ የመሬት ስፋት መጠን በዝርዝር ገልፆ ማስታወቅ አለበት።

ሀ/ አርሶአደሩ በማሳው ላይ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸው ሰብሎች እና የመደበኛ የእርሻ ሥራዎች አቀላቅሎ የሚያመርት እንደሆነ በመጀመሪያ የኢኮኖሚዊ ጠቀሜታ ባላቸው ሰብሎች (በማፈራረቅም ሆነ በማዳበል) የተሸፈነ የመሬት ስፋት ለይቶ ካስታወቀ በኋላ ይህንኑ ከጠቅላላው የአርሶአደሩ የመሬት ይዞታ ላይ በመቀነስ የሚቀረው በሁሉም የመደበኛ እርሻ ሥራዎች የተሸፈነ የመሬት ስፋት መሆኑን ገልፆ ማስታወቅ አለበት።

ለ/ አርሶ አደሩ በማሳው ላይ በዓመት ከአንድ በላይ የሆኑ የኢኮኖሚያዊ ተቀሜታ ያላቸው ሰብሎች በማፈራረቅ የሚያመርት እንደሆነ በየወቅቱ በእያንዳንዱ በተጠቀሱት ሰብሎች የተሸፈነ የመሬት ስፋት ለየብቻቸው ገልፆ ማስታወቅ አለበት።

፲፪. በአርሶ አደር ወይም በከፊል አርብቶ አደር በግል ይዞታነት ተመዝግቦ የነበረ የገጠር መሬት ባለይዞታው ከዚህ አለም በሞት በመለየቱ ወይም ከአካባቢው ከሁለት ዓመታት በላይ በመሰወሩ ህጋዊ ወራሽ የሌለው መሆኑን የታወቀ እንደሆነ የገጠር መሬቱ ባለቤት የማይኖረው በመሆኑ በዚህ ሁኔታ የሚገኝ መሬት በመንግስት

ይዞታ ስር የሚቆይ በመሆኑ መሬቱን የማስተዳደር ኃላፊነት ለቀበሌው አስተዳደር እንዲተላለፍ ይደረጋል፡፡

፲፫. የወረዳ የታክስ አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ያልተሰጣቸው ባለይዞታዎች በራሳቸው ግንዛቤ በአካባቢው የመሬት መለኪያ አንባር ያስታወቁትን የይዞታ ስፋት ወደ ሄክታር በመለወጥ የሚፈለግባቸውን የገቢ ግብር እና የመጠቀሚያ ክፍያ የሚሠላበት ወጥ አሰራር መከተል እንዲቻል በወረዳው ህብረተሰብ ዘንድ የሚታወቁት የገጠር መሬት ስፋት መለኪያ መሣሪዎች ከሄክታር ጋር ያላቸው የእኩሌታ ስሌት ዝርዝር ከወረዳው አስ/ም/ቤት ጋር ተመካክሮ በማዘጋጀት ለቀበሌ አስተዳደር አስቀድሞ የማሳወቅ ኃላፊነት አለበት፡፡

፲፬. አርብቶአደሩ በወረዳው በሚኖርበት ቀበሌም ሆነ በሌሎች ቀበሌዎች ከአንድ በላይ ቤተሰብ የመሠረተ በመሆኑ በባለቤትነት የያዛቸው እንስሳት እርባታ መጠን በየቤተሰብ አንባር ከፋፍሎ ማስታወቅ ከፈለገ ይህንኑ በመግለፅ በየቤተሰቡ ስም ለይቶ ማስታወቅ ይችላል፡፡

፲፭. እያንዳደንዱ አርብቶአደር በባለቤትነት የያዛቸው ቀንድ ከብቶች ብዛት በሙሉ በቀበሌው አስተዳደር ጽ/ቤት ቀርቦ በዝርዝር ለይቶ በመግለፅ የማስታወቅ ግዴታ አለበት፣

፲፮. የክፍያ መሠረታቸው ማስታወቅ በሚገባቸው ወቅት በአካባቢው የሌሉ በመሆኑ ወይም በተለያዩ ማህበራዊ ምክንያቶች ማስታወቅ የማይችሉ ባለይዞታዎች /የእንስሳት ባለቤቶች/ በቀበሌው የሚገኙ እንደሆነ ለአካለ መጠን በደረሱ ቤተሰቦቻቸው ወይም በሞግዚታቸው ወይም በህጋዊ ተወካያቸው ወይም በሀገር ሽማግሌዎችና በጎሳ መሪዎች አማካኝነት የክፍያ መሠረቶቻቸውን ማስታወቅ ይችላሉ፡፡ ይህ ሳይፈፀም በቀረበት ሁኔታ የክፍያ መሠረታቸው በገማች ኮሚቴ ተገምቶ እንዲቀርብ ይደረጋል፡፡

፲፯. የቀበሌ አስተዳደር አርሶአደሩ የሚያስታውቀው የመሬት ይዞታ በእጁ ላይ በሚገኘው የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ወይም አስቀድሞ በአካባቢው በሚታወቅ የይዞታው ስፋት መሠረት እንዲሁም አርብቶ አደሩ የሚያስታውቀው በጎሳው በሚታወቀው በባለቤትንት በያዛቸው የእንስሳት እርባታ ብዛት መሠረት መሆኑን በመከታተል ትክክለኛነቱን ያረጋግጣል፣ ልዩነት ያለው መሆኑን ሲያምንበት በገማች ኮሚቴ ተገምቶ እንዲስተካከል ያደርጋል፡፡

፲፮. ቀበሌው አስተዳደር አስቀድሞ ባዘጋጀው ቀበሌው የግብር ከፋዮች መዝገብ ላይ ከተዘረዘሩት እርሶአደሮችና ከፊል አርብቶአደሮች ወይም አርብቶአሮች መካከል የክፍያ መሠረታቸውን በወቅቱ ያላስታወቁ ያሉ እንደሆነ ከመዝገቡ ላይ በየመንደራቸው ለይቶ በማዘጋጀት የጊዜ ገደብ ከመጠናቀቁ በፊት ቀርበው እንዲያስታውቁ መቀስቀስ አለበት፡፡

፲፱. የቀበሌው አስተዳደር የክፍያ መሠረታቸውን በወቅቱ ያስታወቁ የቀበሌው አርሶአደሮችና አርብአደሮች ያስታውቁትን የመሬት ይዞታ ወይም የእንስሳት እርባታ መጠን ለይቶ በማዘጋጀት የታክስ አስተዳደር ባለሥልጣን በሚያዘጋጀው ቅፅ መሠረት በዝርዝር መዝግቦ የማስታወቂያ የጊዜ ገደብ እንደተጠናቀቀ (በገማች ኮሚቴው የሚቀርበውን ሳይጠብቅ) ወዲያውኑ ለወረዳው አስተዳደር ም/ቤት በመጀመሪያ ዙር የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

፳. በቀጣይ ጊዜያት በየዓመቱ መጀመሪያ በቀበሌው የመሬት ይዞታ ባለቤት መሆን የቻሉ ወይም እንስሳት የማርባት ሥራ የጀመሩ አዳዲስ ግብር ከፋዮች ሲገኙ የመሬት ይዞታው ባለቤት መሆን በቻሉ ወይም እንስሳትን ማርባት በጀመሩ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ በቀበሌው አስተዳደር ጽ/ቤት ቀርበው በክፍያው መሠረት በዝርዝር የማስታወቅ ግዴታ አለባቸው፡፡

፳፩. የቀበሌው ግብር ከፋዮች ይዞታቸው ወይም የእንስሳት ሃብታቸው ሙሉ ለሙሉ ለወራሾች መተላለፉና ወራሾች በውርስ ያገኙትን የገጠር መሬት ወይም የእንስሳት ሃብት በስማቸው ተመዝግቦ ግብር መክፈል መጀመራቸው ተረጋግጦ ወይም በመሬት ይዞታው /በእንስሳቱ/ ባለቤትንት መብት ያለው አካል ባለመኖሩ በመንግስት ይዞታ ሥር እንዲሆን በመደረጉ ምንያት በሙሉ ወይም በከፊል የባለቤትንት መብታቸውን ያጡ መሆኑን ተገልፆ ከግብር ከፋይነት እንዲሠረዙ ከቀበሌው አስተዳደር የሚቀርብ ጥያቄ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችለው ማስረጃ በወረዳው አስተዳደር ም/ቤት ታምኖበት ሲፀድቅ ብቻ ይሆናል፡፡ ይህን ሂደት ተከትሎ ግብር ከፋዮች ከግብር ከፋይነት እንዲሠረዙ የሚቀርበውና የሚታየው በሦስት ዓመት አንድ ጊዜ ብቻ ሆኖ የቀበሌ አስተዳደር የእነዚህን ዝርዝር መረጃ በተገቢው ቅፅ ሞልቶ ለወረዳው አስተዳደር ም/ቤት ወቅቱን ጠብቆ ሲያሳውቅና በአስ/ም/ቤቱ ሲፀድቅ ከወረዳው ባህረ መዝገብ እንዲሠረዙ ይደረጋል፡፡

፵፪. የቀበሌ አስተዳደር የክፍያ መሠረታቸውን በራሳቸው ያስታወቁትንና በቀበሌው ገማች ኮሚቴ የተገመተላቸውን ግብር ከፋዮች ዝርዝር ለወረዳው አስ/ም/ቤት በመጀመሪያ ዓመት አሚልቶ ካቀረበ በቀጣይ አምስት ዓመታት የእነዚህን ግብር ከፋዮች መረጃ በድጋሚ ማቅረብ ሳያስፈልግ ከላይ በንዑስ አንቀፅ ፵ እና ፵፪ መሠረት ልዩነት ሲከሰት ብቻ የተጨመሩትንና የተሰረዙትን ግብር ከፋዮች መረጃ በተገቢው ቅፅ ሞልቶ ለወረዳው አስተዳደር ም/ቤት በየዓመቱ ከመስከረም ፴ በፊት ማቅረብ አለበት፡፡

፵፫.በገጠር መሬት የኢንቨስትምት ሥራ የሚያከናውኑ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ወይም የግል ባለሀብቶች በይዞታቸው ሥር የሚገኝ የገጠር መሬት ስፋት መጠን የለማም ሆነ ያልለማም በሙሉ በየዓመቱ ከሐምሌ ወር መጀመሪያ እስከ መስከረም መጨረሻ መሬቱ በሚገኝት ወረዳ የታክስ አስ/ቅ/ጽ/ቤት ቀርበው ይዞታቸውን የማስታወቅ ግዴታ አለባቸው፡፡

፩ <u>የግብር ከፋዮችን የክፍያ መሠረት የሚገመትበት አሠራር</u>

ሀ) <u>ስለገማች ኮሚቴዎች መቋቋም</u>

በቀበሌው በስማቸው የሚታወቅ የመሬት ይዞታ ቢኖራቸውም ወይም የእንስሳት እርባታ ባለቤት ቢሆኑም በአዋጁ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ክፍያ መሠረታቸው ማስታወቅ ግዴታቸው ያልተወጡ ወይም አሳንሰው ያስታወቁ ሰዎችን ክፍያ መሠረት ለመገመት እንዲቻል የቀበሌው አስተዳደር ማስታወቂያ የጊዜ ደገቡ በተጠናቀቀ በሁለት ቀናት ጊዜ ውስጥ በቀበሌ ደረጃ እና በልማት ቡድን ደረጃ የገማች ኮሚቴዎች እንደሚከተለው ያቋቁማል፡፡

፩ <u>በቀበሌ ደረጃ አንድ የግመታ አስተባባሪ አብይ ኮሚቴ</u>

ሀ) የቀበሌው ሊቀ መንበር ..... (ሰብሳቢ)

ለ) ›› ም/ሊቀ-መንበር ..... (ም/ሰብሳ)

ሐ) ›› ሥራ አስኪጅ ..... (አባልና ፀሐፊ)

መ) ›› ግብርና ልማተ ጣቢያ አስተባባሪ ..... (አባል)

ሠ) ›› የሕዝብ ግንኙነት ኃፊ ..... ››

ረ) ›› ሁለት ታዋቂ ግለሰቦች (አንድ ወንድ አንድ ሴት) …….. (አባል)

፪. <u>የልማት ቡድን ገማች ኮሚቴ</u>

የክፍያ መሠረታቸውን በወቅቱ ያላስታወቁ የመሬት ባለይዞታዎች ወይም የእንስሳት ባለቤቶች በሚገኝባቸው የልማት ቡድኖች በእያንዳንዳቸው አምስት አባት ያሉት ገማች ኮሚቴ ማለትም

ሀ) የልማት ቡድን መሪ ……..... (ሰብሳቢ)

ለ) የንዑስ ቀበሌው የግብርና ል/ተጠሪ …….. (ፀሐፊ)

ሐ) የልማት ቡድኑ አመራር …….. (አባደል)

መ) ሁለት ታዋቂ ግለሰቦች (አንድ ወንድ አንድ ሴት) …….. (አባል)

ሆነው እንዲዋቀር ይደረጋል፡፡

፫ <u>የጎሳ መሪዎችና የቀበሌ አመራር</u>

በአርብቶ አደር አካባቢዎች በየመንደሩ አንድ የጎሳ መሪና አንድ የቀበሌ አመራር ከላይ በንዑስ አንቀፅ ፪ ከተጠቀሱት በተጨማሪነት እንዲካተቱ በማድረግ የግመታ ሥራው በአጭር ጊዜ በማካሄድ መረጃው በየስማቸው አንባር ተዘርዝሮ እንዲቀርብ ያደርጋል፡፡

፬. በአዋጅ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ የክፍያ መሠረት በትክክል ያላስታወቀ ወይም አሳንሶ ያስታወቀ ማንኛውም ሰው ከገማች ኮሚቴው ጋር በመተባበር የክፍያው መሠረት በወቅቱ የማስገመት ግዴታ አለበት፡፡

ለ) <u>የገማች ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት</u>

፩ በልማት ቡድን ደረጃ የተዋቀረ ገማች ኮሚቴ የግመታ ሥራ የሚያከናውነው በዚህ ደንብ የተመለከቱትን ዝርዝር መረጃዎችን ለማቅረብ የሚያስችል ወጥ አሠራር ተከትሎ መሥራት ይጠበቅበታል፡፡

፪ በተለያዩ ምክንያቶች የመሬት ይዞታቸውንና የእንስሳት እርባታቸውን መጠን በወቅቱ ያላስታወቁ (በአካባቢ የሌሎትን ጭምር) እና አሳንሰው ያስታውቁ አርሶአደሮችና አርብቶአደሮች በሚገኙበት መንደር በመዘዋወር የእያንዳንዱ ሰው የክፍያ መሠረት በተያዘለት የጊዜ ሠሌዳ በጋራ በመገመት መረጃው በተገቢው ቅፅ ሞልቶ ለቀበሌው የግመታ አስተባባሪ ኮሚቴ ያቀርባል፡፡

፫. የግመታው ሥራ የሚያከናውነው ስለ ክፍያ መሠረቱ መጠን በመጀመሪያ ለሚመለከተው ባለመብቱ (ባለቤቱ) ወይም ለአካለ መጠን ለደረሰ ቤተሰቡ፣ በመቀጠልም በአካባቢው ለሚኖሩ የሀገር ሽማግሌዎች በመጠየቅ በቂ መረጃ በመሰብሰብ ኮሚቴው ያመነበትን በስምምነት ወይም በድምፅ ብልጫ ይወሰናል፡፡

፬. በልማት ቡድኑ ውስጥ ከዚህ በፊት በግል ይዞታነት የሚታወቁ ቢሆንም በአሁኑ ጊዜ ባለቤት ያልተገኘላቸው መሬቶች ቢኖሩ ስፋታቸውና የሚገኙበት ሁኔታ ዘርዝሮ ለቀበሌው አስተዳደር ያሳውቃል፡፡

፭. በልማታዊ ቡድኑ ከሚገኙ ግብር ከፋዮች የክፍያ መሠረታቸውን አሳንሰው ያስታወቁ መኖራቸው ሲደረስበት መረጃው ለቀበሌው አስተዳደር ከመስጠት ባሻገር የእነዚህን ነዋሪዎች ትክክለኛ የመሬት ይዞታ ስፋት ወይም የእንስሳት እርባት መጠን በመገመት ለቀበሌው አስተዳደር ያቀርባል፡፡

፮. የቀረበው የግዴታ ሥራ በቀበሌው አስተዳደር ሲመረመር ስህተት የተገኘባቸውን አንደገና በመገመት መረጃውን አስተካክሎ በማዘጋጀት ለቀበሌው የግመታ አስተባባሪ ኮሚቴ በሪፖርት ያቀርባል፡፡

፯. በግመታው ሂደት ለመተባበር ፈቃደኛ ያልሆኑት በሥራው ፍጥነትና ጥፋት ላይ አሉታዊ ጫና የፈጠሩ ሰዎች ቢኖር ለህግ እንዲቀርቡ ዝርዝር መረጃ የሚሰጥ መግለጫ ለቀበሌው አስተዳደር ያቀርባል፡፡

ሐ) <u>የግመታ አስተባባሪ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት</u>

፩. የቀበሌ የግመታ አስተባባሪ ኮሚቴ የክፍያ መሠረታቸውን በወቅቱ ያላስታወቁ አርሶአደሮችና አርብሮአደሮች በሚገኙባቸው ልማታዊ ቡድኖች የመሬት ይዞታቸውን ወይም የእንስሳት እርባታቸውን መጠን ለመገመት እንዲያስችል በየልማት ቡድኑ አንድ ገማች ኮሚቴ ያቋቁማል፡፡

፪. በወቅቱ የክፍያ መሠረታቸውን ያላስታወቁ አርሶ አደሮችና አርብቶ አደሮች ከገማች ኮሚቴው ጋር በመተባበር የመሬት ይዞታቸውን ወይም የእንስሳት እርባታቸውን መጠን የማስገመት ግዴታ የተጣለባቸው መሆኑን ተገንዝበው ድጋፍ እንዲሰጡ መመሪያዎችን ያስተላልፋል፡፡

፫. በገማች ኮሚቴ አማካኝነት የሚካሄደውን የግመታ ተግባር ተከታትሎ ይደገፍል፣ ይቆጣጥራል ለሚያጋጥሙ ችግሮች አፋጣኝ መፍትሄ ይሰጣል፣ በበላይነት ይመራል፡፡

፬. በየልማት ቡድኖቹ ከገማች ኮሚቴው የቀረበለትን መርምሮ በማፅቅ መረጃውን አጠናቅሮ ለወረዳው አስተዳደር ም/ቤት በወቅቱ ያቀርባል። ሆኖም በኮሚቴው የቀረበለትን የክፍያ መሠረት ግምት ስህተት ያለበት መሆኑን ሲያምንበት ግመታው እንደገና ተካሄዶ እንዲስተካከል ለገማች ኮሚቴው መመሪያ ይሰጣል።

፭. የክፍያ መሠረታቸውን አሳንሰው ያስታወቁ የቀበሌ ነዋሪዎች መኖራቸው በማናቸውም ጊዜ ሲደርስበት ትክክለኛ የመሬት ይዞታቸውን ወይም የእንስሳት እርባታቸውን መጠን በገማች ኮሚቴ ተገምቶ እንዲቀርብ ያደርጋል።

፮. የቀበሌ የግመታ አስተባባሪ ኮሚቴ አጠቃላይ የግመታ ሥራው መምራት ኃፊነት ያለበት በመሆኑ ገማች ኮሚቴ በማዋቀር፣ ላስታወቁ የመሬት ወይም የእንስሳት ባለቤቶች ዝርዝር ለይቶ ለኮሚቴው በመስጠት፣ ለገማች ኮሚቴው በግመታው የአፈፃፀም ስልት ላይ በቂ ግንዛቤ በማስጨበጥ፣ የጊዜ ሠሌዳ በመወሰን እና አፈፃፀሙን በመከታተልና በመገምገም ለሚያጋጥሙ ችግሮች አፋጣኝ መፍትሄ በመስጠት ተግባሩን የማስፈፀም ኃላፊነት አለበት።

፯. የቀበሌው አስተዳደር በገማች ኮሚቴው የተከናወነው የግመታ መረጃ ስለትክክለኛነቱ የኮሚቴው አባላት በሙሉ በፊርማቸው እንዲያረጋግጡ በማድረግ በአስተባባሪ ኮሚቴ ተገምግሞ ሲታመንበት በግምት የተዘጋጀው ክፍያ መሠረት በየግብር ከፋዮቹ ስም ዝርዝር አንባር ተመልክቶ የታክስ አስተዳደር በሚያዘጋጀው ቅፅ መሠረት የቀበሌው ማህተም አርፎበት በሊቀ መንበሩ ፊርማ ለወረዳው አስ/ም/ቤት በሁለተኛ ዙር ቀርባል።

ክፍል ሦስት

የገቢ ግብር እና የመጠቀሚያ ክፍያ አወሳሰን

፮ የግብር ከፋዮች አመዳደብ እና የሚፈለግባቸውን የመጠቀሚያ ክፍያና የገቢ ግብር ተመን የሚወሰንበት አሠራር

፩. የክልሉ ግብር ከፋይ አርሶ አደሮች በሚያከናውኑት የግብርና ልማት ምርት ውጤቶች ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ላይ ተመስርቶ በሁለት የግብር አከፋፈል ደረጃዎች ተመድበዋል።

ሀ) በአዋጁ አንቀፅ ፪ ከንዑስ አንቀፅ ፲፫ እስከ ፲፮ እና በዚህ ደንብ በአንቀፅ ፪ ከንዑስ አንቀፅ ፱-፲፩ በተመለከተው መሠረት የወረዳው የታክስ አስ/ቅ/ጽ/ቤት ከቀበሌው አስተዳደር የተላለፈውን የክፍያ መሠረት መረጃ በመጠቀም ከቀበሌው የመሬት ባለይዞታዎች መካከል በሚያከናውኑት የግብርና ልማት አንፃር በመስኖ፣ በሙዝ፣ በቡና፣ በጫት፣ በአፕል፣ በበርበሬ ፣በዝንጅብል፣ በኮረሪማና በሌሎች ቅመማ ቅመሞች ሰብሎች በተሸፈነው የመሬት ስፋት አኳያ የኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸው ቅመማ ቅመሞች ሰብሎች አምራች ወይም የመስኖ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይመድባል፡፡

ለ) በሚያከናውኑት የግብርና ልማት አንፃር በዚህ ደንብ አንቀፅ ፪ ንዑስ አንቀፅ ፲፪ መሠረት የሚፈረጁ ወይም በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፩/ሀ በተጠቀሰው ምድብ ሊፈረጁ የማይችሉ የመሬት ባለይዞታ አርሶአደሮች ወይም ከፊል አርብቶቸደሮች የመደበኛ እርሻ ተጠቃሚ እንደሆኑ ይመደባሉ፡፡

፪ የቀበሌው አስተዳደር እና ወረዳው የታክስ አስ/ቅ/ጽ/ቤት በዚህ ደንብ አንቀፅ ፮.፩ መሠረት ለቀበሌው ግብር ከፋዮች የተሰጠውን ምደባ በየሦስት ዓመት ሊያሻሻሉ ይችላል፡፡

፫ ከቀበሌ አስተዳደር የተላለፈውን ግብር ከፋዮች የክፍያ መሠረት መረጃ በመጠቀም ግብር ከፋዮችን ከላይ በንዑስ አንቀፅ ፩ በተመለከተው መሠረት የመመደብ እና የሚፈለግባቸውን የገቢ ግብር እና የመጠቀሚያ ክፍያ መጠን የመተመን ሥልጣንና ተግባር የወረዳው የታክስ አስተ/ቅ/ጽ/ቤት ይሆናል፡፡

፬ የወረዳው የታክስ አስ/ቅ/ጽ/ቤት የገቢ ግብር እና የመጠቀሚያ ክፍያ የመወሰን ተግባር የሚያከናውነው ለየቀበሌው በሁለት ዙር ሆኖ በመጀመሪያው ዙር በአዋጁ የተጣለባቸውን ግዴታ አክብረው የክፍያ መሠረታቸውን በወቅቱና በትክክል ሳያስታወቁ በመቅረታቸው ወይም አሳንሰው በማስታወቃቸው በቀበሌው አስተዳደር የተገመተላቸው ግብር ከፋዮች ይሆናል፡፡

፭ የወረዳው ታክስ አስ/ቅ/ጽ/ቤት የክፍያ መሠረታቸው በቀበሌ ገማች ኮሚቴ ለተገመተላቸው ግብር ከፋዮች በቀረበው መረጃ መሰረት የሚፈለግባቸውን የገቢ ግብር እና የመጠቀሚያ ክፍያ ሲወስን የክፍያቸው መሠረት በወቅቱ ባለማስታወቃቸው ወይም አሳንሰው በማስታወቃቸው የተጣለባቸውን ፳ በመቶ መቀጫ ጭምር አስልቶ በመተመን ለቀበሌው ማስተላለፍ አለበት፡፡ ሆኖም ይህ

መቀጫ የሚጣለው አርሶአደሩ ወይም አርብቶአደሩ የክፍያ መሠረቱ በወቅቱ ሳያስታውቅ በቀረበት ለመጀመሪያ የግብር ዓመት ብቻ ይሆናል፡፡

፮ አንድ አርሶ አደር በገጠር መሬት ላይ ከመደበኛ እርሻ ተጠቃሚነት በተጨማሪ በአዋጅ አንቀፅ ፪ ከንዑስ አንቀፅ ፲፫-፲፮ እና በዚህ ደንብ አንቀፅ ፪ ከንዑስ አንቀፅ ፱-፲፩ ከተጠቀሱት የኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸው የግብርና ልማት ሥራዎች መካከል በሁለቱና ከዚያ በላይ በሆኑ ሰብሎች ወይም በመስኖ ልማት አንድ አራተኛ (1/4) ሄክታርና ከዚያ በላይ በሆነ የመሬት ስፋት ሰብሎችን በማፈራረቅ ወይም በማዳበል ያለማ እንደሆነ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ባላቸው ሰብሎች ተጠቃሚነቱ ተመድቦ የሚፈለግበትን ግብር እና ክፍያ ይተመናል፡፡

፯ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በፈረቃ አጠቃቀም በእያንዳንዱ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ባለው ሰብል በየወቅቱ የተሸፈነ የመሬት ስፋት አንድ ላይ በመደመርና በሰብሎቹ ብዛት በማካፈል አርሶአደሩና በተጠቀሱት ሰብሎች በጣምራ በአማካይ የሸፈነው የመሬት ይዞታ ስፋት ስሌት አንዳር ታይቶ በመመደብ የሚፈለግበትን የገቢ ግብር እና የመጠቀሚያ ክፍያ በዚሁ አንዳር ተሠልቶ ይወሰናል፡፡

፰ ማንኛውም አርሶ አደር በገጠር መሬት ላይ የኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ባላቸው ሰብሎች እና በመስኖ ልማት ከተሸፈነው በተጨማሪ ለመደበኛ እርሻ ሥራ የሚጠቀምበትን ቀሪ የመሬት ይዞታው ለብቻው ተለይቶ በስፋቱ መጠን ለመደበኛ እርሻ ተጠቃሚዎች በተወሰነው የአከፋፈል ሁኔታ አንዳር የሚፈለግበትን ግብር እና ክፍያ ተሰልቶ ከላይ በንዑስ አንቀጽ ስድስት ወይም ሰባት በተመለከተው ስሌት ጋር በመደመር ጠቅላላ መክፈል ያለበትን የመሬት መጠቀሚያ ክፍያና የግብርና ሥራ ገቢ ግብር መጠን ይወሰናል፡፡

፱ በአዋጁ አንቀፅ ፱ ን/አንቀፅ ፪ በተመለከተው ሠንጠረዥ ላይ የተጠቀሰው የአርብቶ አደሩ የቀንድ ከብቶች ብዛት የቀንድ ከብቶቹ ያላቸው የበሬ ዋጋ እኩሌታ ተሠርቶ የተገኘ የበሬ እኩሌታ ብዛት የቀንድ ከብቶች ብዛት ሆኖ ይወሰዳል፡፡

፲ የወረዳ የታክስ አስ/ቅ/ጽ/ቤት አርብቶ አደሩ በዝርዝር ያስታወቀውን የእያንዳንዱ የቀንድ ከብት ብዛት መረጃ መሠረት በማድረግ የበሬ ብዛትን እንዳለ በመውሰድ እና የሌሎች ቀንድ ከብቶች ብዛትን በዚህ ደንብ አንቀፅ ፮ ን/አንቀፅ ፲፩ በተደነገገው መሠረት ከበሬ ዋጋ አንዳር ባለው የእኩሌታ ንጽጽር በማስላት የእያንዳንዱ አርብቶአደር ግብር የሚከፈልበት የቀንድ ከብት እርባታ ብዛት በበሬ እኩሌታ አንዳር የተሠላው ብዛት አጠቃሎ በመደመር

በአዋጅ አንቀፅ ፱/፪ በተመለከተው ሠንጠረዥ መሠረት የሚፈለግበትን የገቢ ግብር መጠን ይወሰናል፡፡

፲፩. እያንዳንዱ የቀንድ ከብት ከበሬ ዋጋ አንፃር ያለው የእኩሌታ ንፅፅር እንደሚከተለው ተወስኗል፡፡

ተ/ቁ	የአስተዳደር አካባቢ	አማካይ የበግና የፍየል እኩሌታ ብዛት ከበሬ ዋጋ አንፃፊ	አማካይ የላም እኩሌታ ብዛት ከበሬ ዋጋ አንፃር	አማካይ የወይፈን እኩሌታ ብዛት ከበሬ ዋጋ አንፃር	አማካይ የጊደር እኩሌታ ብዛት ከበሬ ዋጋ አንፃር
1	የክልሉ አማካይ	8፡1	11፡10	9፡4	9፡5

፲፪. ማንኛውም ሰው የገጠር መሬት ይዞታ የባለቤት መብት ለማስከበር የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር የመያዝ እና በይዞታው ላይ የሚፈለግ የመጠቀሚያ ክፍያና የገቢ ግብር የመክፈል ግዴታዎች በጣምራ አሟልቶ መፈፀም ይኖርበታል፡፡ በመሆኑም ባለይዞታው በአካባቢ እያለ ለሁለት ተከታታይ ዓመታት ከሁለቱ ጣምራ ግዴታዎች በአንዱ ወይም በሌላው ወይም በሁለቱም በሙሉ ወይም በከፊል ግዴታውን ያልተወጣ እንደሆነ በገጠር መሬቱ ላይ የባለቤትነት መብት ሊያቀርብ ወይም ሊያሰከብር አይችልም፡፡ ሆኖም ባለይዞታው በተለያዩ ምክንያቶች በአካባቢው የማይኖር መሆኑን ከተረጋገጠ የጊዜ ገደቡ ከአራት ዓመት ሳይበልጥ ሊራዘም ይችላል፡፡

፲፫. የመሬት ባለይዞታዎች ባስታወቁት መጠንም ሆነ በቀበሌ አስተዳደር በተገመተው የክፍያ መሠረት በመጠቀም ከእያንዳንዱ ግብር ከፋይ የሚፈለግ የገቢ ግብር እና የመጠቀሚያ ክፍያ ተተምኖና ለየቀበሌው ተላልፎ የመሰብሰብ ሥራ እንደተጀመረ የወረዳው የታክስ አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ከቀበሌ የተላለፈውን የክፍያ መሠረት ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ከዚህ ቀደም በየቀበሌው ተተክቶ በወረዳው የግብርናና ገጠር ልማት ጽ/ቤት ውስጥ የሚገኘው የባለይዞታዎቹ የመሬት ይዞታ ስፋት መረጃ ጠይቆ በመውሰድ ማገናዘብ አለበት፡፡

፲፬. የወረዳው የግብርናና ገጠር ልማት ጽ/ቤትም ይህንኑ መረጃ እንዲሰጥ ሲጠየቅ በየቀበሌው አዘጋጅቶ ለወረዳው የታክስ አስ/ቅ/ጽ/ቤት የማስተላለፍ ግዴታ አለበት፡፡

፲፮. ይህ መረጃ ሲገናዘብ የመሬት ይዞታቸውን አሳንሰው ያስታወቁ ባለይዞታዎች የተገኙ እንደሆነ የታክስ አስ/ቅ/ጽ/ቤት በልዩነቱ የሚፈለግ የገቢ ግብር እና የመጠቀሚያ ክፍያ በመተመን እና አሳንሶ በማስታወቅ ፵ በመቶ መቀጫ አክሎ ለየቀበሌ አስተዳደር በማስተላለፍ በተጨማሪነት እንዲሰበሰብ ማድረግ አለበት፡፡ በልዩነት በተገኘ የመሬት ይዞታ ላይ ተጨማሪ የገቢ ግብር እና የመጠቀሚያ ክፍያ ሲሰላ የመሬት ይዞታው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ባላቸው ሰብሎች የተሸፈነ መሆኑን ተጨባጭ መረጃ ካልተገኘ በስተቀር ይዞታው ለመደበኛ እርሻ ሥራ እንደዋለ በማሰብ ይወሰናል፡፡

፲፯. ማንኛውም ግለሰብ የመሬት ይዞታውን ሕጋዊ የኪራይ ውል ስምምነት በመፈፀም በሙሉ ወይም በከፊል ለሌላ አርሶ አደር ወይም ለባለሃብት በጊዜያዊነት በኪራይ ሲያስተላልፍ ይህንኑ ለቀበሌው አስተዳድር ያሳወቀ እንደሆነ ባከራየው የመሬት ስፋትና በተከራይ የመሬቱ አጠቃቀም ሁኔታ አንፃር መከፈል የሚገባውን የመጠቀሚያ ክፍያና የገቢ ግብር የመክፍል ግዴታ በኪራይ ውሉ በተጠቀሰው መሠረት እንዲፈፀም መጠየቅ ይችላል፡፡ በውሉ ላይ ይህንን የመክፍል ግዴታ ተለይቶ ባለተጠቀሰበት ሁኔታ ግን አከራዩ ወይም ባለይዞታው የመክፈል ግዴታ ይኖርበታል፡፡ ሆኖም ተከራዩ በተከራየው የመሬት ስፋትና የአጠቃቀሙ ሁኔታ አንፃር የሚፈለግበትን የመጠቀሚያ ክፍያና የገቢ ግብር በአከራዩ ስም በመክፈል ከኪራይ ሂሳብ ላይ እንዲቀናነስ የማድረግ መብት ይኖረዋል፡፡

፲፰. የመሬቱ ባለይዞታ ሳይሆን የሌላን ሰው የገጠር መሬት ይዞታ በአደራ ወይም በሞግዚትነት የሚያስተዳድር ማንኛውም ሰው በአዋጁ መሠረት በመሬቱ የሚፈለግ ግብር እና ክፍያ በባለይዞታው ስም የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡ በዚህ ሁኔታ የከፈለው ሂሳብ ከባለይዞታው መልሶ የመቀበል ወይም በወጪ እንዲያዝለት የማድረግ መብት ይኖረዋል፡፡

፲፱. የገጠር መሬት ባለይዞታዎች ወይም የእንስሳት እርባታ ባለቤቶች በሞት ሲለዩ ወራሾች ከክፍያው መሠረት የሚፈለግ የገቢ ግብር እና የመጠቀሚያ ክፍያ የመክፈል የጋራና የተናጠል ግዴታ አለባቸው፡፡

፲፱. በማንኛውም ግለሰብ ስም በባለቤትነት በተመዘገበ የገጠር መሬት ይዞታ ላይ መከፈል የሚገባው መጠቀሚያ ክፍያና የገቢ ግብር መክፈል ግዴታ በአዋጁ አንቀፅ ፳፩ ከተጠቀሰው ሁኔታ በስተቀር በሌላ ማናቸውም ሁኔታ እንዲቀር ማድረግ አይቻልም፡፡

፳. በገጠር መሬት በማናቸውም የግብርና ልማትም ሆነ በኢንዱስትሪ ልማት ሥራ የተሠማራ ማንኛውም የመንግስት የልማት ድርጅት ወይም የግል ባለሃብት ለመሬት ኪራይ ክፍያ የእፎይታ ጊዜ መብት የተሰጠው ለመሆኑ የወረዳው የታክስ አስ/ቅ/ጽ/ቤት በተጨባጭ

መረጃ ካልተረጋገጠ በስተቀር በገጠር መሬት ይዞታው ላይ የሚፈለግበትን የኪራይ መጠን መሬቱን ከተረከበበት ጊዜ ጀምሮ በአከባቢው የኪራይ ተመንና በመሬት ኪራይ ስምምነት ውሉ መሠረት በማስላት በየዓመቱ ከጥቅምት ወር ጀምሮ የውሳኔ ማስታወቂያ አዘጋጅቶ ለሚመለከተው የመሬት ባለይዞታው እንዲደርሰው ያደርጋል፡፡

፵፩. በገጠር መሬት የግብርናም ሆነ የኢንዱስትሪ ልማት ለማካሄድ መሬት ከተሰጠው አካል ጋር የኪራይ ውል ስምምነት የሚፈፅም የመንግስት ተቋም ውሉ እንደተፈፀመ የውሉ አንድ ቅጂ ለወረዳው የታክስ አስ/መ/ቤት በማስተላለፍ የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡

፵፪. የተጠቀሰው የገጠር መሬት ለባለሃብቱ ርክክብ የሚፈፀም አካል ርክክብ ከመፈፀሙ በፊት በውሉ ዘመን ከጠቅላላው የመሬቱ ስፋት ለባለሃብቱ ከሚፈለገው የኪራይ ሂሳብ ውስጥ ፱ በመቶ በቅድሚያ መከፈሉን የማረጋገጥ ግዴታ አለበት፡፡

ክፍል አራት

የገቢ ግብር እና የመጠቀሚያ ክፍያ

የአከፋፈልና የአሰባሰብ ሥርዓት

፷. የገቢ ግብር እና የመጠቀሚያ ክፍያ አሰባሰብና ለወረዳው ገቢ የሚደረግበት አሠራር

፩ ከቀበሌ ግብር ከፋይ አርሶአደሮች ወይም አርብቶአደሮች የሚፈለግ የገቢ ግብር እና የመጠቀሚያ ክፍያ እንዲሰበሰብ በአዋጁ ከተፈቀደለት የቀበሌ አስተዳደር በስተቀር በሌላ በማናቸውም ባልተፈቀደለት ሰው ሊሰበሰብ አይችልም፡፡

፪ በክልሉ መንግስት የከተማነት ደረጃ በተሰጣቸው ከተሞች ዙሪያ የሚገኙና በከፊል ወይም በሙሉ በከተማው ስር በታቀፉ የገጠር ቀበሌዎች ውስጥ ነዋሪ የሆኑ የመሬት ባለይዞታዎች በአዋጁ በተወሰነው መጠን መሠረት ከይዞታቸው ላይ የሚፈለግባቸውን የገቢ ግብር እና የመጠቀሚያ ክፍያ ለቀበሌ አስተዳደር የከፈሉትን ለከተማው የታክስ አስተዳደር ገቢ መደረግ አለበት፡፡

፫ የቀበሌው አስተዳደር (ግብር ሰብሳቢ) ከቀበሌው ግብር ከፋዮች የሚሰበሰበው የገቢ ግብር እና የመጠቀሚያ ክፍያ በእያንዳንዱ ግብር ከፋይ ስም አንፃር ከወረዳው አስተዳደር በሚተላለፍለት ተመን መሠረት ሆኖ ግብሩ ሲሰበሰብ ለዘርፉ ተለይቶ የተዘጋጀው የገቢ ደረሰኝ በሶስት ቅጂ በማዘጋጀት አንደኛውን ቅጂ ለእያንዳንዱ ግብረ ከፋይ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡ ሁለተኛው ቅጂ ለወረዳው የታክስ

አስ/ቅ/ጽ/ቤት የሚተላለፍ ሲሆን ሶስተኛው ቅጂ ከጥራዙ ጋር ቀርቶ ለወረዳው የፋይ/ኢኮ/ል/ጽ/ቤት ተመላሽ ይደረጋል፡፡

፬ ግብር ሰብሳቢነት ደረሰኙን ሲያዘጋጅ የከፋዩን ሙሉ ስምና አድራሻ፣ የተቀበለው ገንዘብ መጠን በአሀዝና በፊደል እና የተሰበሰበበት ቀንና ዓመት ምህረት በካርቦን ኮፒ እንዲሁም የሰብሳቢው ስምና ፊርማ ያለካርቦን በጭቃ ቀለም እስክሪብቶ ሊነበብ በሚችልበት ሁኔታ በመሞፍ በደረሰኙ ሦስቱም ቅጠሎች ላይ አንድ ዓይነት የተሟላ መረጃ ማስፈር ግዴታ አለበት፡፡ በሦስቱ ቅጠሎች ላይ የሚሰፍረው መረጃ በፍፁም መለያየት የለበትም፡፡

፭ ግብር ሰብሳቢው ደረሰኝ ሲያዘጋጅ ስህተት ቢፈጠርበት በደረሰኙ ሦስቱም ቅጠሎች ላይ በትልቁ "X" ምልክት በማድረግና ‹‹**የተበላሸ**›› የሚል ፅሁፍ በማስፈር ሦስቱንም ቅጠሎች በማጠፍ በደረሰኝ በሚቀጥለው ቅጠል ላይ መረጃውን እንደገና አስተካክሎ በመሞፍ ለከፋዩ ቆርጦ ይሰጣል፡፡ በመሆኑም ስርዝ ድልዝ ያለበትን ደረሰኝ ለከፋዩ በፍፁም መስጠት አይኖርበትም፡፡

፮ ከዚህ ለዘርፉ ተለይቶ ከተዘጋጀው የገቢ ደረሰኝ በስተቀር ከአርሶአደሩ እና ከአርብቶአደሩ የሚሰበሰብ የገቢ ግብር እና የመጠቀሚያ ክፍያ በማናቸውም ምክንያት በሌላ ደረሰኝ ወይም ያለደረሰኝ አይሰበስብም፡፡

፯ የወረዳ የታክስ አስ/ቅ/ፅቤት የደረሰኝ አያያዝ፣ አጠቃቀምና አዘገጃጀት አስመልክቶ ለቀበሌ ግብር ሰብሳቢዎች ማብራሪ በመስጠት በቂ ግንዛቤ እንዲጨብጡ ከማስቻል ባሻገር አፈፃፀማቸውን ተከታትሎ የመደገፍ ኃላፊነት አለበት፡፡

፰ ማንኛውም የቀበሌ ግብር ሰብሳቢ፡-

A በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የሰበሰበውን ገንዘብ እስከ ብር ፳፪ (ሁለት ሺ ብር) ከሆነ በየወሩ የመጨረሻ ቀናት ጊዜ፣

E በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የተሰበሰበው ገንዘብ ከብር ፳፪ (ሁለት ሺ ብር) በላይ ከሆነ የወሩ የመጨረሻ ቀን ሳይጠበቅ ወዲያውኑ ከተሰራበት ደረሰኝ ጋር ለወረዳው የታክስ አስ/ቅ/ት/ቤት በማቅረብ አስመርምሮ ገንዘቡን ገቢ ማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

፱ የወረዳው የታክስ አስ/ቅጽ/ቤት የዘመኑን የገቢ ግብር እና የመጠቀሚያ ክፍያ ያልከፈሉ ግብር ከፋዮች በአዋጅ አንቀፅ ፲፮ ንዑስ አንቀፅ ፭ በተደነገገው መሠረት የገቢው መሰብሰቢያ የጊዜ ገደብ ከተጠናቀቀ በኋላ ባለው የአንድ ወር ጊዜ ውስጥ

በመለየት ለቀበሌው አስተዳደር እና ለወረዳው አስተዳደር ም/ቤት በማሳወቅ እዳው በሚፈለግባቸው ግለሰቦች ላይ ተገቢው ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድባቸው ያደርጋል፡፡

፲ የቀበሌው አስተዳደር የሚፈለግባቸውን የገቢ ግብር እና የመጠቀሚያ ክፍያ በአዋጁ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ሳይከፍሉ የቀሩ አርሶአደሮች ወይም አርብቶአደሮች ያሉ እንደሆነም ስም ዝርዝራቸውም በየመንደሩ የቀሩ አርሶአደሮች ወይም አርብቶአደሮች ያሉ እንደሆነ ስም ዝርዝራቸውን በየመንደሩ ለይቶ በማዘጋጀት ለቀበሌው ም/ቤት ጉባኤ አቅርቦ እንዲታወቁና እንዲመከርበት ያደርጋል፡፡ ከዚህ በኋላም ካልከፈሉ በቀበሌው ማህበራዊ ፍ/ቤት ክስ ተመስርቶባቸው በሕግ አስገዳጅነት እንዲከፈሉ ያደርጋል፡፡

፲፩. የወረዳው አስተዳደር ም/ቤት እና የቀበሌው አስተዳደር በመተባበር የየቀበሌው ማህበራዊ ፍ/ቤት አባላት ሥልጠና በመስጠት በየቀበሌው የሚፈለግባቸውን የገቢ ግብር እና የመጠቀሚያ ክፍያ በወቅቱ ባልከፈሉ ግለሰቦች ላይ በሕጉ መሠረት ክስ ተመስርቶባቸው በሕግ አስገዳጅነት እንዲከፈሉ የማድረግ የጋራ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

፲፪. የወረዳው ታክስ አሰ/ቅ/ጽ/ቤት በወረዳው ከሚገኙ የገጠር ቀበሌዎች መካከል በዘመኑ ከግብር ከፋዮቹ መሰብሰብ የሚገባውን የገቢ ግብር እና የመጠቀሚያ ክፍያ በወቅቱ አጠናቀው ያልሰበሰቡ እና ሌሎች የአፈፃፀም ችግሮች ያለባቸው ቀበሌዎች ተለይተው እንዲታወቁ ለወረዳው ም/ቤት ጉባኤ አቅርቦ እንዲመከርበትና የመፍትሄ አቅጣጫ እንዲቀመጥለት ማድረግ አለበት፡፡

፲፫. በገጠር መሬት ላይ ከተከናወኑ ማናቸውም የኢንቨስትምት ስራዎች የሚፈለግ የኪራይ ክፍያ የሚሰበሰበው በወረዳው የታክስ አሰ/ቅ/ጽ/ቤት በኩል በመደበኛ የግብር እና የታክስ መሰብሰቢያ ደረሰኝ በመጠቀም ሆኖ የገቢው አሰባሰብ አፈፃፀም በክልሉ የገቢ ግብር ሕግ መሠረት ይሆናል፡፡

፰ <u>የደረሰኝ ስርጭትና አመላለስ፣</u>

፩ <u>የደረሰኝ ስርጭት አሠራር</u>

ሀ) የወረዳው የፋ/ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት በክልሉ መንግስት ለዘርፉ ተለይቶ የተዘጋጀውን የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ከሁለት ወራት በፊት በማቅረብ ከወረዳው አስ/ም/ቤት በሚገለፅለት የስም ዝርዝር መሠረት የመሰብሰቢያ ጊዜ ከመድረሱ በፊት ለየቀበሌው አስተዳዳሪ ወይም ሥራ አስኪያጅ በሕጋዊ ደረሰኝ ወጪ አድርጎ ያሠራጫል፡፡

ለ) የወረዳው አስ/ም/ቤት የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ሊሰጣቸው የሚችሉ የየቀበሌው አስተዳዳሪ ወይም ሥራ አስኪያጅ የስም ዝርዝር መረጃ ለወረዳው የፋይ/ኢኮ/ል/ጽ/ቤት እጅግ ቢዘገይ የመሰብሰቢያ ጊዜው ከመድረሱ ከአንድ ወር በፊት በየዓመቱ ማስተላለፍ አለበት፡፡

ሐ) የቀበሌው አስተዳዳሪ ወይም ሥራ አስኪያጅ የደረሰኝ ጥያቄው በፅሁፍ በማቅረብ የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞችን የመሰብሰቢያ ጊዜ ከመድረሱ ከአንድ ወር በፊት በወረዳው የፋ/ኢ/ል/ጽ/ቤት በመቀረብ በሕጋዊ ደረሰኝ ወጪ አድርጎ መረከብ አለበት፡፡

መ) የወረዳው የፋ/ኢ/ልማት ጽ/ቤት የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞችን ለቀበሌ አስተዳደር ሲያሠራጭ የደረሰኙን ብዛትና ተከታታይ ቁጥር (ንምራ) እና የተረከበው ሰው ስም በየቀበሌው አንባር ተመዝግቦ የሚያዝበት አሠራር ይመሠረታል፡፡ የደረሰኙ ሥርጭት እንደተከናወነ ወዲያውኑ የተሠራጨው ደረሰኝ ብዛት፣ ተከታታይ ቁጥር (ንምራ) እና ወጪ አድርጎ የተረከበው ሰው ስም በየቀበሌው በመዘርዘር ለወረዳው የታክስ አስ/ቅ/ጽ/ቤት ያስተላልፋል፡፡

ሠ) የወረዳው የታክስ አስ/ቅ/ጽ/ቤት ከወረዳው የፋይ/ኢኮ/ል/ጽ/ቤት የተላለፈለትን የደረሰኝ ሥርጭት መረጃ መዝግቦ በመያዝ አመላለሱን የመከታተልና የመቆጣጠር ኃላፊነት አለበት፡፡

ረ) በየዘመኑ ለቀበሌ አስተዳደር የሚራጨው የገቢ ግብር እና የመጠቀሚያ ክፍያ የመሰብሰቢያ ደረሰኝ ብዛት በዓመቱ ለቀበሌው የሚያስፈልገውን ጠቅላላ የደረሰኝ ብዛት በሶስት ዙር በመክፈል የሚሰጥ ሆኖ በመጀመሪያው ዙር አንድ ሦስተኛ ያህሉ ብቻ በመስጠት ለቀበሌው ተጨማሪ ደረሰኝ ሊሰጥ የሚችለው መጀመሪያ የወሰዳቸው ደረሰኞችና የተሰበሰበው ገንዘብ ገቢ መደረጉን በወረዳው የታክስ አስ/ቅ/ጽ/ቤት ሲረጋገጥ ብቻ ይሆናል፡፡

ሰ) የወረዳ አስተዳደር ም/ቤት፣ የፋይ/ኢ/ልማት ጽ/ቤት እና የታክስ አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ለቀበሌው የተሠራጨው የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ በትክክልና በአግባቡ ሥራ ላይ እየዋለ መሆኑን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ የተናጠልና የጋራ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

፪. <u>የደረሰኝ አመላለስ አሠራር</u>

ሀ) የቀበሌ አስተዳደር ከቀበሌው የመሬት ባለይዞታዎች ወይም አርብቶ አደሮች የተሰበሰበ የገቢ ግብር እና የመጠቀሚያ ክፍያ ወደ ወረዳ የታክስ አስ/ቅ/ጽ/ቤት ገቢ ሲያደርግ የተሰራባቸውን ደረሰኞች ጭምር ይዞ በመቅረብ ካስመረመረ በኋላ የተጠናቀቁት ለወረዳው የፋን/ኢኮ/ል/ጽ/ቤት በደረሰኝ ተመላሽ ያደርጋል፡፡

ለ) የወረዳው የታክስ አስ/ቅ/ጽ/ቤት የቀበሌ ገቢ ሰብሰቢ የሰበሰበውን ገንዘብና የተሰራበት ደረሰኝ ይዞ ሲቀርብ የተሠራባቸው ደረሶኞች ሁለተኛ ቅጂ ከጥራዙ ለይቶ በመሰብሰብ በጥንቃቄ መያዝና ለመረጃ ምንጭ እንዲውል ማድረግ አለበት፡፡

ሐ) በአዋጁ ላይ የተቀመጠው የገቢ መሰብሰቢያ ጊዜ ከተጠናቀቀ ከሁለት ወራት በኋላ ለቀበሌ አስተዳደር ተሠራጭተው የተሰራባቸውም ሆኑ ያልተሠራባቸው ደረሰኞች በሙሉ ለወረዳው የፋይ/ኢኮ/ል/ጽ/ቤት ተመላሽ መደረግ አለባቸው፡፡ ሆኖም በተለያዩ ምክንያቶች የዘመኑን መሠረተ ግምት አጠናቅቀው ያልሰበሰቡ ቀበሌዎች ሲያረጋግጥ ለውዝፍ አሰባሰብ እንዲያገለግል አንድ ጥራዝ ደረሰኝ ተመላሽ ሳይደረግ በቀበሌው አስተዳደር እጅ እንዲቆይ ሊደረግ ይችላል፡፡

መ) የወረዳ የታክስ አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት በቀበሌ አመራር የቀረበለትን የተሠራባቸው የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች መርምሮ ትክክለኛነቱን በማረጋገጥ ገንዘቡን በሕጋዊ የገቢ ደረሰኝ ከተረከበ በኋላ ደረሰኞች ለወረዳው የፋይ/ኢኮ/ል/ጽ/ቤት ተመላሽ እንዲያደረጉ ያስተላልፍል፡፡ በግብር ዓመቱ መጨረሻ ማለትም በሰኔ ወር መጨረሻ ወይም በሌላ በማናቸውም ምክንያት ተመላሽ በሚደረግ በአንድ በተሠራበት የገቢ ደረሰኝ ጥራዝ ውስጥ ያልተሠራባቸው ቅጠሎች ያሉት እንደሆነ በሦስቱም ቅጠሎች ላይ በትልቁ "X" ምልክት በማድረግና "የተሰረዘ" የሚል ፅሁፍ በማስፈን ለሌላ አገልግሎት እንዳይውል ማድረግ ይኖርበታል፡፡

ሠ) ለቀበሌ አስተዳደር ተሠራጭተው የተሰራባቸው ደረሰኞች ለፋይ/ኢኮ/ል/ጽ/በት ተመላሽ ከመደረጋቸው በፊት በታክስ አስ/ቅ/ጽ/ቤት የውስጥ ኦዲተር ተመርምሮ የተሰበሰበውን ገቢ የተደረገው የገንዘብ መጠን እና የተሰበሰበው የደረሰኙ ቁጥሮች ከ-እስከ በመጥቀስ የወስጥ ኦዲተሩ ስም ፊርማና የመ/ቤቱ ማህተም በተሠራበት የደረሰኙ የመጨረሻ ቅጠል ጀርባ ላይ የተመለከተ መሆኑን መረጋገጥ አለበት፡፡

ረ) የወረዳው የፋ/ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤትና የታክስ አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት በበጀት ዓመቱ ለየቀበሌው የተሰረጨው ተመላሽ ያልተደረጉትን ደረሰኞች ብዛትና ተከታታይ ቁጥር በመዘርዘር ለወረዳ አስተዳደር ም/ቤት በጋራ ያሳውቃሉ፡፡ ደረሰኞችንም ለማስመለስ ከወረዳው አስተዳደር ም/ቤት ጋር በመተባበር ግዴታቸውን ባልተወጡ የቀበሌ አመራሮች ላይ ተገቢውን ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድባቸው ያደርጋሉ፡፡

ሰ) በአንድ ቀበሌ የገቢ ግብር እና የመጠቀሚያ ክፍያ ለመሰብሰብ ከወረዳው የፋይ/ኢ/ል/ጽ/ቤት ደረሰን ወጪ አድርጎ የተረከበ አመራር በተለያዩ ሁኔታዎች ካለበት የኃላፊነት ደረጃ ሲለቅ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የሰበሰበውን ገንዘብ በወረዳው የታክስ አስ/ቅ/ጽ/ቤት ቀርቦ በማስመርመር ገቢ ማድረግና የተረከባቸውን የገቢ ደረሰኞ በሙሉ ለወረዳው የፋይ/ኢኮ/ል/ጽ/ቤት ተመላሽ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡ የወረዳው አስተዳደር ም/ቤትም ይህ ሁኔታ ሲከሰት ተከታትሎ የማስፈፀም ኃላፊነት አለበት፡፡

፱. <u>የመቀጫ አጣጣልና አሰባሰብ፣</u>

፩ እያንዳንዱ አርሶ አደር ወይም አርብቶ አደር የክፍያው መሠረት የሆነው የመሬት ይዞታው ወይም የእንስሳት እርባታው ቁጥር በትክክል ካላስታወቀ ወይም አሳንሶ ካስታወቀ ፭ በመቶኛ እና ወይም ክፍያውን በወቅቱ ሳይከፍል ከዘገየ በየወሩ ፪ በመቶ እስከ ፶፭ በመቶ ድረስ ባልተወጣው ግዴታ አንፃር በአዋጁ የተጣለውን መቀጫ ተሠልቶ በተጨማሪነት እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

፪ ባለመስታወቅ የሚጣል መቀጫ የሚሰላው በወረዳው የታክስ አስ/ቅ/ጽ/ቤት ሲሆን ሳይከፈል በዘገየበት የሚጣል መቀጫ የሚሠላው በቀበሌው አስተዳደር አማካኝነት ይሆናል፡፡

፫ ግብሩንና ክፍያው ሣይፈፀም ከዘገየ የመቀጫው አጣጣል በዘገየበት ለእያዳንዱ ወር፡-

ሀ) ለመጀመሪው አንድ ቀንና የዚህ ከፊል ለሆነው የወሩ ቀናት ፪ በመቶ

ለ) ለሚቀጥለው ተጨማሪ ወር በየወሩ ፪ በመቶ ይሰላል፡፡

ሐ) ሆኖም ጠቅላላ በዘገየበት የሚጣለው መቀጫ መጠን ከክፍያውና ከግብሩ ፶፭ በመቶ አይበልጥም፡፡

፬. የክፍያው መሠረት በሙሉ ወይም በከፊል ሳያስታወቅ የቀረ በቀበሌው አስተዳደር በተገመተው ወይም በልዩነት በተገኘው የክፍያ መሠረት አንፃር ከግለሰቡ የሚፈለግ የገቢ ግብር እና የጠቀሚ ክፍያ ከተሰላ በኋላ ፳ በመቶ መቀጫ በተጨማሪነት ታክሎበት እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

፭. የቀበሌ ግብር ሰብሳቢ ከወረዳው ከተላለፈለት ግብር ከፋዮች ስም አንፃር ከተመለከተው የገቢ ግብር እና የመጠቀሚያ ክፍያ ተመን መጠን አሳንሶ ቢሰበሰብ ሳይሰበሰብ የቀረው የግብር እና የክፍያ መጠን በራሱ የመክፈል ግዴታ ያለበት ከመሆኑም በላይ ፲ በመቶ መቀጫ በተጨማሪነት እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

፮. የቀበሌ ግብር ሰብሳቢ በአዋጁና በዚህ ደንብ የተጣለበትን ኃላፊነትና ግዴታዎች ሣይፈፅም ከቀረ ወይም የተከለከሉ አሠራሮችን ፈፅሞ ከተገኘ ለአብነትም የሰበሰበውን ገንዘብ ለወረዳው በወቅቱ ገቢ ሳያደርግ ከቀረ፣ የተረከበውን የገቢ መሰብሰቢ ደረሰኞች በወቅቱ ተመላሽ ሳያደርግ ከቀረ፣ ባልተፈቀደ ደረሰኝ ወይም ያለደረሰኝ የገቢ ግብሩ እና ክፍያው ሰብስቦ ከተገኘ፣ በደረሰኙ ሦስቱ ቅጠሎች ላይ የተለያየ መረጃ አስፍሮ ከተገኘ ወይም ስርዝ ድልዝ ያለበት ደረሰኝ ለግብር ከፋዩች ሰጥቶ ከተገኘ በድርጊቶቹ በወንጀል ተጠያቂ ይሆናል፡፡ ስለሆነም የተጠቀሱት ድርጊቶች ተፈፅመው ሲገኙ የወረዳው አስ/ም/ቤት፣ የወረዳው የፋይ/ኢኮ/ል/ጽ/ቤት እና የወረዳው የታክስ አስ/ቅ/ጽ/ቤት ተገቢው መረጃዎች በማሰበሳሰብ በፈፃሚው አካል የወንጀል ክስ በመመስረት ሕጋዊ ቅጣት እንዲያገኝ የማድግ የጋራና የተናጠል ኃላፊነት አለባቸው፡፡

፲. <u>የመቀጫ አነሳስ አሠራር፣</u>

፩. ማንኛውም አርሶ አደር ወይም አርብቶ አደር የመሬት ይዞታውን ስፋት ወይም የእንስሳት እርባታውን ቁጥር በትክክል ባለማስታወቅ ወይም አሳንሶ በማስታወቅ እና አዘግይቶ በመክፈል ከተጣለበት ጠቅላላ መቀጫ እስከ ፭ በመቶ ሊነሳለት የሚችል ሆኖ ይህ ተፈፃሚ የሚሆነው ግብር ከፋዮቹ የሚፈለግባቸውን ትክክለኛ የገቢ ግብር እና የመጠቀሚያ ክፍያ እስከ ሚያዝያ ፴ አጠናቀው ከከፈሉ ብቻ ይሆናል፡፡

፪. እስከ ግንቦት ፴ ለሚከፍሉት ፲፭ በመቶ እና እስከ ሰኔ ፴ ለሚከፈሉት ደግሞ ፳ በመቶ መቀጫ ይነሳላቸዋል፡፡

፫. ከሰኔ ወር በኋላ ለሚከፍሉት ከፉ በመቶ ላይ በየወሩ ፤ በመቶ እየተቀነሰ በሚገኘው ምጣኔ መቀጫው የሚነሳላቸው ሆኖ እስከ ሚቀጥለው ዓመት ታህሳስ ወር ሳይከፍሉ ቀርተው ከጥር ወር ጀምሮ ለሚከፍሉት የተጣለባቸውን መቀጫ የማይነሳላቸው በመሆኑ ሙሉ በሙሉ እንዲከፍሉ ይደረጋል፡፡

፬. የገቢ ግብር እና የመጠቀሚያ ክፍያ መሠረት ባለማስታወቅ ወይም አሳንሶ በማስታወቅ እና አዘግይቶ በመክፈል የተጣለ መቀጫ የማንሳት ሥልጣን የወረዳው የታክ አስ/ቅ/ጽ/ቤት እና የቀበሌው አስተዳደር የጋራ ኃላፊነት ይሆናል፡፡

፭. የቀበሌው አስተዳደር ገቢ ሲሰበስብ እንደየግብር ከፋዩ የአከፋፈል ጊዜ አንጻር በዚህ ደንብ በተወሰነው ምጣኔ መሠረት እንዲቀር ያደርገው (የተነሳው) የመቀጫ መጠን በየግብር ከፋዩ ስም በመዝርዘር ለወረዳው ታክስ አስ/ቅ/ጽ/ቤት አቅርቦ ማፅደቅ ይኖርበታል፡፡

፮. የገጠር መሬት ላይ በግብርናም ሆነ በኢንዱስትሪ ልማት በተሠማሩ የኢንቨስትመት ባለቤቶች ላይ የተጣለው መቀጫ የሚነሳው በክልሉ የገቢ ግብር ሕግ በተወሰነው መሠረት በመስፈርት ይሆናል፡፡

<u>፮፮. ከመሬት መጠቀሚያ ክፍያና ከግብርና ሥራ ገቢ ግብር ነፃ ስለመሆን፣</u>

፩ በድርቅ፣ በወረርሽኝ በሽታ፣ በጎርፍ አደጋ፣ በመሬት መንሸራተት ፣በጦርነት፣ በእሳት አደጋ በመሬት መንቀጥቀጥ፣ በስደትና በሌሎችም ሰው ሠራሽና የተፈጥሮ አደጋ ምክንያቶች አርብቶ አደሩም ሆነ አርሶ አደሩ ጉዳት ከደረሰበት ወይም ከቀዬው ከተፈናቀለ ይህንኑ በየደረጃው በሚገኝ በሚመለከተው የመንግስት አካል ከተረጋገጠ ለሚመለከታቸው ግብር ከፋዮች ብቻ ይህ ሁኔታ ከተከሰተበት ዓመት ጀምሮ አደጋው ያስከተለው ጉዳት መወገድ እስከሚረጋግጥበት ጊዜ ድረስ ከሚፈለግባቸው የገቢ ግብር እና የመጠቀሚያ ክፍያ ነፃ እንዲሆኑ ሊያደርግ ይችላል፡፡

፪ ከአቅም በላይ የሆነ አደጋ በመድረሱ የሚቀርብ ነፃ የመሆን ጥያቄ ተፈፃሚ የሚሆነው ከላይ በንኡስ አንቀፅ ፩ በተገለፀው ዓይነትና መጠን መሠረት የደረሰው አደጋ ትክክለኛ ለመሆኑ ከቀበሌው አስተዳደር ጀምሮ በተዋረድ እስከ ዞን/ልዩ ወረዳ አስተዳደር ቀርቦ በዞኑ/በልዩ ወረዳው አስ/ም/ቤት ተቀባይነት አግኝቶ ሲፀድቅ ብቻ ይሆናል፡፡

፫. በግል ይዞታነት ተመዝግቦ ግብር ከሚከፈልበት የገጠር መሬት ውስጥ በተፈጥሮ አደጋ ምክንያት ወይም በሌላ የተጎዳ መሬት በወረዳው የግብርና የገጠር ልማት ጽ/ቤት እውቅና ለተወሰነ ዓመት ከሰውና ከእንስሳት ንኪኪ ተከልሎ እንዲያገግም ከተደረገ በዚህ ሁኔታ እንዲቆይ ለተደረገው የመሬት ስፋት መጠንና ለሚቆይበት ዓመታት ብቻ ከግብር ነፃ እንዲሆን ሊደረግ ይችላል፡፡

፬. ለኢንቨስመንት ተግባር በዋለ የገጠር መሬት ላይ የሚፈለግ የኪራይ ክፍያ ምህረት ሊደረግ የሚችለው በክልሉ የገቢ ግብር ሕግ የግብር ምህርት ሰለሚደረግበት ሁኔታ በተወሰነው መሠረት ብቻ ይሆናል፡፡

፭. ማንኛውም በግል ይዞታነት ያልተመዘገበና ለማናቸውም አገልግሎት የዋለ ወይም ሊውል የሚችል የገጠር መሬት የወል መሬትን ጨምሮ በመንግስት ይዞታ ሥር የሚገኝ በመሆኑ በዚህ ሁኔታ ለሚቆይበት ጊዜ ሁሉ በአዋጁ የተጣለው መሬት መጠቀሚያ ክፍያና የግብርና ስራ ገቢ ግብር አይከፈልበትም፡፡

፮. ማንኛውም የገጠር መሬት ባለይዞታ በሚመለከተው የመንግስት አካል በመሬቱ የመጠቀም መብቱን ለህዝብ ጥቅም ሲባል መሬቱን በከፊል ወይም በሙሉ እንዲያጣ የተደረገ ከሆነ በተቀነሰው የገጠር መሬት ስፋት መጠን ብቻ በአዋጁ ከተጣለው የመሬት መጠቀሚያ ክፍያና የግብርና ሥራ ገቢ ግብር ከመክፈል ግዴታ ነፃ ይሆናል፡፡

፯. በሠፈራና በመንደር ምስረታ ምክንያት አዲስ የመሬት ይዞታ በሠፈሩበት አካባቢ የተሰጣቸው አርሶ አደሮች እስከ ሦስት ዓመት ድረስ በዚህ የገጠር መሬት ይዞታቸው ላይ በአዋጁ ከተጣለባቸው የመጠቀሚያ ክፍያ እና የገቢ ግብር ከመክፈል ግዴታ ነፃ ይሆናሉ፡፡

፰. አርብቶ አደሩ ለእንስሳት እርባታው ግጦሽ በጋራ የሚጠቀምበት በገጠር መሬት በአዋጁ ከተጣለው መጠቀሚያ ክፍያ ነፃ እንዲሆን ተደርጓል፡፡

፱. አርብቶ አደሩ ከሚያረባቸው እንስሳት መካከል የጋማ ከብቶች በሙሉ በአዋጁ ከተጣለው የገቢ ግብር ነፃ እንዲሆን ተደርጓል፡፡

፲. በክልሉ በገጠር መሬት የልማት ሥራዎች የሚያከናውኑ ኢንቨስተሮች ከሚፈለግባቸው የመሬት ኪራይ ክፍያ ለተወሰኑ ዓመታት ነፃ የሚሆኑት በክልሉ ኢንቨስትመንት ሕግ በተሰማሩበት የልማት ሥራ አንፃር ነፃ የተደረጉ ሲሆን ይህ ጊዜ ሲጠናቀቅ የሚፈለግባቸውን የመሬት ኪራይ የመክፈል ግዴታ አለባቸው፡፡

፲፩. ከመሬት ኪራይ ክፍያ የእፎይታ ጊዜ የተሰጣቸው መሆኑን በመረጃ ከተረጋገጠ የተሰጣቸው መብት መቆጠር የሚጀምርበት መሬቱን ከተረከቡበት ጊዜ ጀምሮ ለተፈቀደላቸው ዓመታት ከመሬት ኪራይ ክፍያ ነጻ የተደረጉ ሲሆን ይህ ጊዜ ሲጠናቀቅ የሚፈለግባቸውን የመሬት ኪራይ የመክፈል ግዴታ አለባቸው፡፡

፲፪ በክልሉ የኢንቨስትመንት ሕግ ባለሃብቶች የተሠማሩበትን የኢንቨስትመንት ሥራ በሚያስገኝ ፋይዳ፣ በሚጠይቀው የካፒታል መጠን፣ ምርት ለመሰብሰብ በሚፈጀው ጊዜ፣ በአከባቢው ባለው መሠረት ልማት አቅርቦት... ወዘተ አንፃር እየተመዘነ ለተወሰኑ ዓመታት ከገቢ ግብር ነፃ እንዲሆን የሚፈቀድበት አሠራር እና የመሬት ኪራይ የእፎይታ ጊዜ የሚሰጥበት ሁኔታ በተናጠል ለየብቻ የሚታዩ በመሆኑ ኢንቨስተሮች ሁለቱንም መብቶች የተሰጣቸው መሆኑን በጣምራ እንዲታይ የሚቀርብ ጥያቄ ሊስተናገድ አይችልም፡፡

ክፍል አምስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፲፫. አቤቱታ የሚቀርብበት አሠራር

፩. እያንዳንዱ አርሶአደር ወይም ከፊል አርብቶአደር ወይም አርብቶአደሮች ትክክለኛ የክፍያ መሠረቱን በቀበሌው አስተዳደር ጽ/ቤት በጊዜ ገደብ እንዲያስታውቅ በአዋጁ የተጣለበትን ግዴታ ሳይወጣ በመቅረቱ የክፍያው መሠረት (የመሬት ይዞታው ስፋት ወይም የእንስሳት እርባታው ብዛት) በቀበሌው ገማች ኮሚቴ ተገመቶ በቀረበው መረጃ መሠረት የተወሰነለትን የገቢ ግብር እና የመጠቀሚ ክፍያ መጠን አግባብ አይደለም በሚል ቅሬታ ከተሰማው አቤቱታ የማቀረብ መብት አለው፡፡

፪ ሆኖም በመሬት ይዞታ ላይ አቤቱታ ማቅረብ ያለበት የግብር ውሳኔውን በቀበሌው አስተዳደር ለህብረተሰብ ከተገለፀለት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ በየቀበሌው ለተቋቋመው የመሬት አስተዳደር አጠቃቀም ኮሚቴ ይሆናል፡፡

፫ በተገመተለት የእንስሳት እርባታ ብዛት ላይ ቅሬታ የተሰማው አርብቶአደሮ የግብር ውሳኔው ለቀበሌው ህብረተሰብ ከተገለፀበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ አቤቱታውን ለቀበሌው ማህበራዊ ፍ/ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡

፬. የመሬት ባለይዞታው ወይም የእንስሳት እርባታ ባለቤቱ ወይም ተወካዩ ባስታወቀው የክፍያ መሠረት ላይ አቤቱታ ሊቀርብበት አይችልም።

፭. የቀበሌው መሬት አስተዳደር ኮሚቴ ወይም የማህበራዊ ፍ/ቤት አቤቱታው በቀረበለት በ፲፭ ቀን ጊዜ ውስጥ ገማች ኮሚቴውንና አቤቱታ አቅራቢውን አነጋግሮ ጉዳዩን በማጣራት ውሳኔ በመስጠት ውሳኔው ለአቤቱታ አቅራቢውና ለቀበሌው አስተዳደር በፅሁፍ ያሳውቃል።

፮. የቀበሌው አስተዳደርም በአቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ የተሰጠውን ውሳኔ በገቢ ግብርና በመጠቀሚ ክፍያው መጠን ላይ ለውጥ የሚያስከትል ከሆነ ውሳኔው በደረሰው በ፲ ቀናት ውስጥ ለወረዳው የታክስ አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ያስተላልፋል።

፯. ታክስ አስ/ቅ/ጽ/ቤትም የደረሰውን የተስተካከለ የክፍያ መሠረቱን በመጠቀም ውሳኔው በደረሰበው በ ፲ ቀናት ጊዜ ውስጥ የገቢ ግብርና የመጠቀሚያ ክፍያው መጠን አንደገና አስተካክሎ በመወሰን ለቀበሌው አስተዳደር ያስተላልፋል።

፰. የቀበሌው የመሬት አስተዳርና አጠቃቀም ኮሚቴ ወይም የቀበሌው ማህበራዊ ፍ/ቤት የቀረበለትን አቤቱታ መርመሮ በገማች ኮሚቴ የቀረበውን የይዞታ ስፋት ስህተት ያለው መሆኑን ደርሶበት እንዲስተካከል በሚወሰንበት ጊዜ የስህተቱ ምንጭ፣ የተገናዘቡ የሰነድና የሰው ማስረጃዎች የተደረሰበት ድምዳሜ በዝርዝር ገልፆ ለቀበሌው አስተዳደር ማሳወቅ አለበት።

፱. የቀበሌው የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴ ወይም የቀበሌው ማህበራዊ ፍ/ቤት በሚሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ የሚቀርበው በመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሕግ ወይም በማህበራዊ ፍ/ቤት አሠራር መሠረት መብቱ ለሚፈቅድለት አካል ይሆናል።

፲፫. ስለማበረታቻ አበል አከፋፈል፣

፩. በአዋጅ አንቀፅ ፲፰ በተደነገገው መሠረት የቀበሌው ግብር ሰብሳቢ ከሰበሰበው የግብር፣ የክፍያና የመቀጫ ጠቅላላ ድምር ላይ በኮሚሽን መልክ እንዲከፈል ከተፈቀደው ፫ በመቶ የማበረታቻ አበል ውስጥ 0.5 (ግማሽ) በመቶ ለቀበሌው አስተዳደር ለሥራ ማስኬጃነት (ለጽ/መሣሪያዎች ግዢ) እንዲውል ይደረጋል።

፪. የቀበሌው አስተዳደር ከቀበሌው ግብር ከፋዮች ከሰበሰበው የገቢ ግብር፣ የመጠቀሚያ ክፍያ እና የመቀጫ ሂሳብ ጠቅላላ ድምር ላይ ከተፈቀደው ፫ በመቶ ኮሚሽን ውስጥ ፪.፭ በመቶ ለግብር ሰብሳቢዎች የማበረታቻ አበል እንዲውል እና 0.5 (ግማሽ)

በመቶ ለቀበሌ አስተዳደር ለጽ/መሳሪያዎች ግዢ እንዲውለው ክፍያ የሚፈፀመው በቀጥታ ከተሰበሰበው ገቢ በመቀነስ በህጋዊ ሠነድ ለአምጪው ወዲያውኑ አስፈርሞ በመስጠት ሆኖ ወጪው ከውስጥ ገቢ እንደተፈቀደ የወጪ በጀት ተቆጥሮ ከታክስ አስ/ቅ/ጽ/ቤት በሚቀርብ ወጪ ማስረጃ መጠን በወረዳው የፋይ/ኢኮ/ል/ጽ/ቤት አማካኝነት በወጪ በጀት ተፈቅዶ ቅ/ጽ/ቤቱ ሂሳብ ሪፖርት እንዲተካ ይደረጋል፡፡

፫. ይህ ሁኔታ ሲፈፀመ የወረዳው የታክስ አስ/ቅ/ጽ/ቤት የቀበሌው ግብር ሰብሳቢ የሰበሰበውን ገንዘብ መርምሮ ትክክለኛነቱን በማረጋገጥ ሙሉ ለሙሉ በገቢ በመመዝገብና ለኮሚሽኑ ክፍያ ወጪ ሠነድ አዘጋጅቶ ከውስጥ ገቢ እንደተፈቀደው ወጪ በመውሰድ በወጪ በጀት መዝግቦ ሂሳቡን ለወረዳው የፋይ/ኢኮ/ል/ጽ/ቤት ሪፖርት ያቀርባል፡፡

፬. ለቀበሌው ግብር ሰብሳቢዎች በአዋጅ ላይ በተገለፀው መሠረት የማበረታቻ ክፍያው የሚፈፀመው ከቀበሌው ግብር ከፋዮች የሰበሰቡትን ገንዘብ ለወረዳው በትክክል ገቢ ማድረጋቸውና ደረሰኙን ጭምር ተመላሽ ማድረጋቸውን ተመርምሮ ሲረጋገጥ ብቻ ይሆናል፡፡

፲፬. ስለመዛግብት አያያዝ

፩. የቀበሌው አስተዳደር በቀበሌው በስማቸው የተመዘገበ መሬት ይዞታ ባለቤት የሆኑ አርሶ አደሮች ስም ዝርዝርና የመሬት ይዞታቸው ስፋት በመሬት አጠቃቀማቸው ሁኔታ (የመደበኛ እርሻ ተጠቃሚ ወይም የኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸው ሰብሎች ተጠቃሚ በሚል) ሁለት ምድብ በመክፈል ወይም የእንስሳት እርባታ ባለቤት የሆኑ አርብቶ አደሮች ስም ዝርዝርና ያላቸው የእንስሳት እርባታ ብዛት እንዲሁም የሚገኙበት መንደር፣ የሚፈለግባቸው የገቢ ግብር እና የመጠቀሚያ ክፍያ መጠን፣ የከፈለበት ቀንና የደረሰኝ ቁጥር የሚመዘገብበት ባህረ መዝገብ በቀበሌው ሥራ አስኪያጅ ዘንድ አንዲያዝ መደረግ አለበት፡፡

፪. የወረዳው ታክስ ቅ/ጽ/ቤት የእያንዳንዱ አርሶ አደር ወይም አርብቶ አደር የክፍያ መሠረት መረጃ፣ በየዘመኑ የሚፈለግባቸው የተወሰነው የገቢ ግብር እና የመጠቀሚያ ክፍያ መጠን፣ የተከፈለውን ግብር እና የክፍያ መጠን፣ የተከፈለበት ቀንና የደረሰኝ ቁጥር የሚሰበሰበት (የሚሰበሰብበት) ደረሰኝ ሁለተኛ ቅጂ ላይ በየጊዜው በማወራረስ ወቅታዊ መረጃ አጠናቅሮ መያዝ አለበት፡፡

፲. የወረዳ የፋ/ኢ/ልማት ጽ/ቤት የግብርና ሥራ ገቢ ግብር እና የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያ መሰብሰቢያ ደረሰኞች ሥርጭትና አመላለስ መከታተያ መዝገብና በማወራረስ የደረሰኞች አጠቃቀም ሕጋዊነት ማረጋገጥ አለበት፡፡

፲፩. <u>የመረጃ ልውውጥ እና የአሰባሰብ አፈፃፀም ሪፖርት አቀራረብ፣</u>

፩. የወረዳው የታክስ አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ከወረዳው አስተዳደር ም/ቤት የተላለፈለትን መረጃ መሠረት በማድረግ በወረዳው ውስጥ ከሚገኙ ቀበሌዎች በመደበኛ እርሻ ተጠቃሚነት እና የኢኮኖሚ ጠቀሜታ ባላቸው ሰብሎች አምራችነት ወይም በመስኖ ተጠቃሚነት የተመደቡትን አርሶ አደሮች ብዛት እና ያላቸው የመሬት ይዞታ ስፋት የሚገልፅ መረጃ በየቀበሌው በመዘርዘር ለዞኑ የታክስ አስተዳደር ጽ/ቤት ያስተላልፋል፡፡ የዞኑ የታክስ አስ/ቤትም ያገኘውን መረጃ በየወረዳው በማጠናቀር ለክልሉ የታክስ አስተዳደር ባለስልጣን የተጠቃለለ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

፪. የቀበሌው አስተዳደር በገቢ አሰባሰብ እና በደረሰኝ አወሳሰድና አጠቃቀም ሂደት ያለው አፈፃፀም እንዲሁም ያጋጠሙ ችግሮችና የመፍትሄ ሃሳቦችን በመግለፅ ለወረዳው አስተዳደር ም/ቤት ለፋ/ኢ/ልማት ጽ/ቤት ወይም ለታክስ አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት በየወሩ ሪፖርት ማቅረብ አለበት፡፡

፫. የወረዳው የታክስ አስ/ቅ/ጽ/ቤት በበኩሉ ከላይ የተመለከተውን ሪፖርት ከሁሉም ቀበሌዎች ሰብስቦ በማጠቃለል በወረዳው መሰብሰብ የሚገባውን የዘመን መሠረተ ግምት መጠን፣ የተሰበሰበውንና ያልተሰበሰበውን ቀሪ የገቢ ግብር እና የመጠቀሚያ ክፍያ መጠን በየቀበሌው በመዘርዘር እና ያጋጠሙ ችሮችና የተሰጡ መፍትሄዎችን በማካተት በወር፣ በሩብ ዓመት፣ በግማሽ ዓመትና በየዓመቱ ለዞን የታክስ አስ/ዋና ቅ/ጽ/ቤት ሪፖርት ማስተላለፍ አለበት፡፡

፬. የዞን የታክስ አስተዳደር ዋና ቅ/ጽ/ቤት እና የልዩ ወረዳ የታክስ አስ/ቅ/ጽ/ቤት በዞን/በልዩ ወረዳው መሰብሰብ የሚገባውን የዘመን መሠረት ግምት መጠን፣ የተሰበሰበውንና ያልተሰበሰበው ቀሪ የገቢ ግብር እና የመጠቀሚያ ክፍያ መጠን በየወረዳው (በየቀበሌው በመዘርዝር እንዲሁም በአሰባሰብ ሂደት ላይ ያጋጠሙ ችግሮችና የተሰጡ የመፍትሄ ሃሳቦችን በመግለፅ ለክልሉ የታክስ አስተዳደር ባለሥልጣን በየሩብ ዓመት፣ በግማሽ ዓመትና በዓመቱ መጨረሻ የተጠቃለለ ሪፖርት ማቅረብ አለበት፡፡

፲፮. <u>የመተባበር ግዴታ</u>

ማንኛውም ሰው ይህን ደንብና ደንቡን ተከትለው የሚወጡት የአፈፃፀም መመሪያዎች ሥራ ላይ በማዋል ረገድ የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

፲፯. <u>ስለተጠያቂነት</u>

ማንኛውም ሰው በዚህ ደንብ የተጣለበትን ግዴታዎች ተላልፎ ሲገኝ አግባብ ባለው ሕግ ይቀጣል፡፡ ስለሆነም የወረዳው አስ/ም/ቤት፣ የወረዳው የፋይ/ኢኮ/ል/ፍ/ቤት እና የወረዳው የታክስ አስ/ቅ/ጽ/ቤት ተገቢው መረጃዎች በማሰባሰብ በፈፃሚው አካል ላይ ተገቢውን ክስ በመመስረት ሕጋዊ ቅጣት እንዲያገኝ የማድረግ የጋራና የተናጠል ኃላፊነት አለባቸው፡፡

፲፰. <u>ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሀኔች</u>

ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር በደንቡ በተመለከቱ ጉዳዮች ተፋፃሚነት አይኖረውም፡፡

፲፱. <u>መመሪያ የማውጣት ሥልጣን፡-</u>

የክልሉ የታክስ አስተዳደር የሥራ አመራር ቦርድ ለዚህ ደንብ መልካም አፈፃፀም የሚረዳ መመሪያ ማውጣት ይችላል፡፡

፳. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

ይህ ደንብ ከመውጣቱ በፊት ያልተሰበሰበ ውዝፍ የገቢ ግብር እና የመጠቀሚያ ክፍያ በአዋጅ ቁጥር 91/89 እና አዋጁን ለማስፈፀም በወጡ መመሪያዎች መሠረት እንዲሰበሰብ ይደረጋል፡፡

፳፩. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል መስ/ም/ቤት ከፀደቀበት ከዛሬ ጥቅምት 20 ቀን 2001 ዓ/ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡

ሀዋሳ ጥቅምት 20, 2001 ዓ/ም

ሸፈራው ሸጉጤ

የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል መንግስት ርዕሰ መስተዳድር